# ቤዛነት በሙላት፡ በደስታ

ዛሬ ማታ ደግሞ፡ በተወዳጁ ጌታችን በኢየሱስ፡ ከሙታን በተነሳው በእግዚአብሔር ልጅ ስም ሰላምታ ሳቀርብላችሁ፡ ደስ ብሎኛል። ስገባም ሕልውናው ቀድሞ እዚህ ተገኝቷል፡ ዛሬ ማታ፡ “ከምናደርገው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ፡” እጅግ አብዝቶ ሲያደርግ ለማየት፡ እየጠበቅን ነው፡ ይህም እግዚአብሔር፡ ከበረከቱ በእኛ ላይ በማፍሰስ፡ በመካከላችንም ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ያደርጋል።

2 ባለፉት ሁለት ምሽቶች ስናገር ነበር... እሁድ ማታ የፈውስ አገልግሎት የነበረን ይመስለኛል፡ ሰኞ ማታ ደግሞ ስሰብክ ነበር። እሳውቄም... እሁድ ጧት፡ በተበርናክሉ ውስጥ፡ አንድ ርዕስ ጀምሬ ነበር። የሕዝቡም ቁጥር፡ ትንሽ ከፍ እስኪል እየጠበቅን ባለበት በዚህ ጊዜ፡ የውስጤን ስሜት፡ ትንሽ ብገልጽ ብዬ አሰብኩ። እ...

3 ከነዚህ ቀናት በአንዱ፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ቢረዳኝም፡ በ—በርከት ያሉ ስብሰባዎች እንዲኖሩን እፈልጋለሁ እነዚያም... ዝም ብላችሁ ገብታችሁ የምትሰብኩበት ወይም መጽሐፍ ቅዱስ የምታስተምሩበት፡ የመሠዊያ ጥሪ የምታደርጉበት፡ ወደ መሠዊያው ወርዳችሁም ለሰዎች የምትጸልዩበት፡ የጥንቱ-ዘመን ባፕቲስቶች እናደርግ እንደነበረው ዓይነት እንዲኖሩኝ እፈልጋለሁ። [አንድ ሰው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] “አሜን” ሲሉ የሰማኋቸው፡ ሁለት ባፕቲስቶችን ብቻ ናቸው። ታዲያ ዛሬ ማታ፡ ሁላችሁም የት ናችሁ?

አንድ ሰው፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ባፕቲስት ነበርክ እንዴ” አለኝ?

እኔም፡ “አዎ፡” አልኩት።

4 በአንድ ወቅት፡ እዚሁ አርካንሳስ እየሰበክሁ ነበር። አንድ ሰው፡ የቀድሞ ሰው፡ ተፈወሰ። እሱ... በእነርሱ ዘንድ... እሱ ናዝሪን ነበር። በሚቀጥለው ቀን፡ ምርኩዞቹን በጀርባው አዝሎ፡ እንዲህ የሚል—የሚል ምልክት ለጥፎበት፡ በከተማው ውስጥ ይዘዋወር ነበር፡ “እግዚአብሔር ትላንት ማታ፡ ከዚህ ላይ አውርዶኛል።” በጣም ክፉኛ ሽባ ነበር። በሊትል ሮክ ውስጥ ነበረ። ለበርካታ ዓመታት በዚያ ሁኔታ ላይ ይኖር ነበር። ኮፍያውን አውልቆ አስቀምጦ፡ ከኮፍያው ውስጥ እርሳሶችን እየሸጠ፡ ስለሚዘዋወርም፡ ሁሉም ሰው ያውቀው ነበር። ሁሉም ሰው ስለሚያውቀውም፡ በከተማይቱ ውስጥ፡ ታላቅ ነገር ማድረግ ጀመረ።

5 ከጥቂት ምሽቶች በኋላ፡ እየሰበክሁ ሳለ፡ እርሱም—እርሱም ተነሳ። “አንድ ደቂቃ፡ ወንድም ብራንሃም፡ አንድ ነገር ብጠይቅህ ቅር ይልሃል፡” አለኝ?

“አይ፡ ጌታዬ፡” አልኩት።

6 እርሱም፡ “መልካም፡” አለ፡ “ስታስተምር ስሰማህ—ስሰማህ፡ ናዝሪን እንደሆንክ አውቄ ነበር።” አክሎም፡ “ከዚያም እዚህ አካባቢ ያሉትን የጴንጤቆስጤ ሰዎች በሙሉ አየሁ፡ አንድ ሰውም የጴንጤቆስጤ ሰው እንደሆንክ ነገረኝ።” አክሎም፡ “ከጥቂት ጊዜ በፊት ደግሞ፡ ባፕቲስት እንደሆንክ፡ ስትናገር ሰምቼሃለሁ።” “ይህ አልገባኝም፡” አለኝ።

7 እኔም፡ “መልካም፡ ይህ ቀላል ነው። እኔ ጴንጤቆስጤ ናዝራዊ ባፕቲስት ነኝ” አልኩት። አዎን። ልክ ነው። እኛ ዝም ብለን… እናምናለን።

8 ኦህ፡ ወዳጆች፡ እኔ ለማንኛውም የቤተክርስቲያን የሐይማኖት ተቋም አባል አይደለሁም፡ ሆኖም የሁሉም አባል ነኝ። ይህንን ሰጀምር፡ “ክርስቶስ ራሴ ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ መጽሐፌ ነው። ዓለም ደግሞ ቤተክርስቲያኔ ነች፡” ብዬ ነበር። ስለዚህ፡ ያ ነው—ያ ነው እስክሞት ድረስ መሆን የምፈልገው።

9 አሁን፡ በአንድ ወይም በሁለት ምሽቶች ውስጥ፡ የፈውስ አገልግሎትን እንደገና ለመጀመር እንሞክራለን፡ ይህን ሰናገኝ… እርግጥ ነው፡ እነዚህን አልጋዎችና ቃሬዛዎች እዚህ ዙሪያ ተዘርግተው ሳይ፡ የሆነ ነገር ማየት እፈልጋለሁ። እዚህ ሉዊስቪል፡ ኬንታኪ ውስጥ የሆነ ነገር እንዲከሰት እጅግ ጓጉቻለሁ፡ ምክንያቱም ይህ የገዛ ትውልድ ግዛቴ ነው።

10 ኬንታኪ ውስጥ፡ ጥሩ የምትሉት ዓይነት፡ ጥሩ ሰብሰባ አድርጌ አላውቅም። ይህንንም የምለው ለማንቋሸሽ አስቤ አይደለም። በብዙ ቦታዎች፡ ብዙ መጥፎ ስብሰባዎች—አጋጥመውኛል። ሆኖም፡ ማለቴ፡ እዚሁ የገዛ ቤቴ ውስጥ፡ በጣም ከባድ ነው። እ… እሱን መሰበር በጣም ከባድ ነው። ለምን እንደሆነ አላውቅም። ሆኖም ኢየሱስ፡ “በገዛ አገሩ” ብሎ ስለተናገረ፡ እንዴት እንደሚሆንም ስለገለጸ፡ ምናልባትም—እንደዚያው ሆኖ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ነገር ግን በጣም ብዙ አስደናቂ ተአምራትን ለማየት ችለን አናውቅም።

11 ከአንድ ወይም ሁለት ዓመት በፊት፡ ጀፈርሰንቪል ውስጥ፡ አገልግሎት ነበረኝ፡ ዳሩ ግን ሴትዮዋ ከዚህ ከኬንታኪ ዙርያ ከሆነ ቦታ የመጣች ነበረች። ከእግሮቿ ወደ ታች፡ ማለቴ፡ ከዳሌዋ እስከ እግሮቿ ድረስ፥ እንደ፡ እንደ ኖራ ሆና ነበር። ለአስራ ሰባት ዓመታትም፡ አልተራመደችም—ነበር። በዚያ ምሽት ብዙዎቻችሁ እዚያ ነበራችሁ፡ ሁኔታውንም ታስታውሳላችሁ። እሷም ቀጥ ብላ በመነሳት ከተበርናክሉ ወደ ውጭ ወጣች፡ ሳትቸገር።

12 አሁን፡ እዚህ ሉዊስቪል ውስጥ የሆነ ነገር እንዲጀመር እፈልጋለሁ፡ እዚህ ውብ በሆነችው ትልቅ ከተማ ውስጥ የድሮ-ዓይነት ሪቫይቫል ሲካሄድ ማየት እመኛለሁ።

13 እንደ ሌሎቹ ከተሞች ሁሉ ከተማ ነች፥ እጅግ ክፉ ነች። ያ እውነት መሆኑን ታውቃላችሁ። ኬንታኪን እያንቋሸሽኩ አይደለም፥ ምክንያቱም፡ እኔም፡ ኬንታኪዊ ነኝ። መልካም። ነገር ግን—ነገር ግን እውነት ነው። ክፉ ነው። ይህ የውስኪዎችና የመጠጥ ፋብሪካዎች ሁሉ መኖሪያ ነው፡ ክፉ መሣሪያዎችና፡ ሁሉም ነገሮች፡ እዚሁ ሉዊስቪል፡ ኬንታኪ አካባቢ ይከሰታሉ፡ ስለዚህ ይህ የሰይጣን ዙፋን ነው።

14 ነገር ግን ሁላችንም በአንድነት ከሆንን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ልንሰባብረው እንችላለን። ልክ ነው። ኃይላችንን በአንድነት አሰተባብረን መግፋት አለብን።

15 ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ በሀገሪቱ ውስጥ በጣም ታዋቂ የሆነ ወንጌላዊ፡ እዚህ ስላሉት አገልግሎቶች፡ ሲናገር ነበር። እርሱም፡ “መልካም፡ ነገሩ እንዲህ ነው” አለ። እንዲህ አለ፡ “ወደ አንዲት ከተማ ስገባ፡ በመላው ሀገሪቱ ያለው

ሁሉ ስብሰባዎቼን ስፖንሰር ማድረግ አለበት አለበለዚያ አልሄድም። አዎን። እንዴታ፡ እስኪ አስቡት። እዚሁ ሉዊስቪል ውስጥ ምናልባት ሰልሳ ወይም ሰባ ትልልቅ የባፕቲስት አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ይመስለኛል። አያችሁ? ሜቶዲስቶችስ? አሰበሪ እዚህ ላይ በመሆኗ፥ ይህች የሜቶዲስት ከተማ ነች። ያ ሰው ፕሬስባይቴሪያንና ሌሎችንም ይቅርና፡ ከሜቶዲስቶችና ከባፕቲስቶች ብቻ፡ ወደዚህች ከተማ ቢመጣ ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር?

16 አሁን እዚህ ከተማ ውስጥ ስንት ሙሉ-ወንጌል አብያተ ክርስቲያናት አሉ? እዚህና እዚያ የሆነ ቦታ ላይ ያሉ ሁለት ወይም ሦስት ትናንሽ ሚሲዮኖች፡ ትናንሽ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ናቸው፡ እርስ በርሳቸውም፡ ጦርነት ውስጥ ናቸው።

17 ስለዚህ ስትገቡ፡ በአገልግሎታችሁ ጥንካሬ ላይ መቆም አለባችሁ። ልክ ነው። ሌላው ቀርቶ... ሁሉም ሰው ፖለቲካ ውስጥ እንደሚገባ ነው። ጌታ የሚልከውን ማንኛውም ነገር ለመቀበል፡ የአገልግሎታችሁ ጥንካሬ ይወስነዋል። ያን አካሄድ እወደዋለሁ። ወንድሜ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ መቆያዬና፡ መታመኛዬ ባይሆን፡ የምታመንበት ሌላ ምንም ነገር የለኝም። ልክ ነው። እ... በጽኑ ዓለት፡ በክርስቶስ ላይ፡ እቆማለሁ፥ ሌላው መሠረት ሁሉ፡ ለእኔ የሚያሰጥም አሸዋ ነው። በፖለቲካ ተጎትተው ከመጡ አሥር ሺህ ሰዎች ይልቅ፡ መልእክቱን እንዲሰሙ እግዚአብሔር እንደላካቸው ለማውቃቸው አምስት ሰዎች ብሰብክ እመርጣለሁ። ልክ ነው።

18 አንድ ሰው በጥንቱ-ዓይነት መለወጥ ተለውጦ፡ በመሠዊያው ፊት ተንበርክኮ ኡ-ኡ ሲል ባይ እመርጣለሁ፡ አሥር ሺህ ሰዎች ቆመው፡ “መልካም፡ እሞክረዋለሁ፡” ሲሉ ከማየት ይልቅ። ልሞክረው? እርሱ የሚሞከር ክርስቶስ አይደለም። እርሱ የሚቀበሉት ነው። ብትኖሩም ብትሞቱም፡ ብትሰጥሙም ብትዋጡም፡ በማንኛውም ሁኔታ ተቀበሉት። ልክ ነው።

19 ዛሬ ማታ፡ ለአሥር ሺህ ሰዎች ብጸልይና፡ ጠዋት ላይ ሁሉም ቢሞቱ፥ የእግዚአብሔር ቃል ትክክል መሆኑን አምኜ፡ ነገ ማታ ተመልሼ እዚህ ለታመሙት እጸልያለሁ። ልክ ነው።

20 እየሞትኩ ብሆንና፥ ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት የሞቱ፡ ያን ያህል ጊዜ በዘላለም ውስጥ የቆዩ አምስት ሺህ ሰዎች፡ ተነስተው ወደ ምድር ቢመጡና፡ እንዲሁም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አትመነው። እርሱ ትክክል አይደለም። አትመነው። እኛ—እኛ አምነነው፡ ሄድን፥ አልተሳካልንም” ቢሉኝ።

21 እኔ ግን አሁንም፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ ልሙት” እላለሁ። ልክ ነው። አምነዋለሁ። ያም ሙሉ ልቤ ነው፡ ሁሉም ነገሬ የተተከለው በዚያ ላይ ነው። በሙሉ ልቤም አምነዋለሁ፡ በእርሱም እተማመናለሁ።

22 ህዝቡን እወዳለሁ። እናንተን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎችን እወዳችኋለሁ። ከእናንተም ጋር ትከሻ-ለ-ትከሻ ሆኜ፡ ሸክሙን ለመሸከም እፈልጋለሁ።

23 አሁን፡ ዛሬ ማታ፥ ትላንት ማታ እንደተናገርኩት፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ዛሬ ማታ፡ ትንሽ እናገራለሁ። ረዘም ላለ ጊዜ አቆይቻችሁ፡ ላደክማችሁ አልፈልግም፡ ምክንያቱም እየጠበቅን ያለነው...

24 ለዚህ ስብሰባ በጌታ ፊት ያቀረብኩት እንደ በግ ጠጉር ያለ ምልክት አለኝ። እዚሁ ከተማ ውስጥም ስብሰባውን የሚያንቀሳቅስ አንዳች ነገር እግዚአብሔር ያደርጋል ብዬ እየጠበቅሁ ነው። ጸልዩ፡ የበኩላችሁንም ድርሻ ተወጡ፥ ከዚያም፡ ፍርድ ሲመጣ፡ ሁላችንም ቆመን የበኩላችንን ድርሻ ተወጥተናል ማለት እንችላለን።

25 በዘጸአት ምዕራፍ 20 ውስጥ፡ ከቁጥር 7 ጀምሮ፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ በጣም... መልካም፡ እጅግ አስደናቂ ባይሆንም፡ ግን—ጥሩ ርዕስ ላይ፡ ለጥቂት ጊዜያት፡ መናገር እፈልጋለሁ። ባለፈው እሁድ፡ በጀፈርሰንቪል ተበርናክል ውስጥ ባለው የሰንበት ትምህርት ቤት፡ “ቤዛነት በደም፡” በሚል፡ ጀምረናል።

26 ለምን ይህን እዚህ እንደማደርግ ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ እያደረግኩ ያለሁት ይሄንን ነው። ብዙዎቻችሁ በፈውስ አገልግሎት ውስጥ ስሰብክ አይታችሁኝ እንደማታውቁ ትናገራላችሁ፡ ዳሩ ግን ዓላማ አለው። ነፍሳት ተሰብረው ወደ መሠዊያው ቢመጡ፡ ለሉዊሰቪል በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አገኛለሁ ብዬ አስባለሁ፡ ልክ ነው፡ ማለትም ሰዎች በእውነት በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክከው ሲጸልዩ።

27 ከዚህም፡ ሌላ፡ ደግሞ፡ የምትጾሙና፡ የምትጸልዩ፡ ብዙ ወዳጆች፡ ለምትጸልዩለት ነገር ለመጨበጥ የምትፈሩ አላችሁ። ልክ ነው። አያችሁ? መልካም፡ አብሮት የሚሄድ ሥራ ከሌላችሁ በስተቀር፡ መጾምና መጸለይ ምንም አይጠቅማችሁም። በዓለም ላይ ያላችሁ፡ እምነት ሁሉ፡ ምንም አይጠቅማችሁም ወደ ውጭ ወጥታችሁ፡ ፊት-ለ-ፊት ተጋፍጣችሁ፡ ካልወሰዳችሁት በስተቀር። በቃ። ወደፊት መሄድ አለባችሁ። እንዲሁ፡ ወጥታችሁ ማድረግ ብቻ ነው ያለባችሁ። ለምንም ነገር ስትጠይቁ፡ ሂዱና ውሰዱት። እግዚአብሔር የእናንተ ነው ሰላለ፡ ከእሱ ያነሰ ምንም ነገር አትቀበሉ። የጠየቃችሁትን ተቀበሉ። ያንን አድርጉና፡ እንዴት እንደሚሆን እዩ። አዎን። ወደኋላ አፈግፍጋችሁ፡ “መልካም፡ ሁለተኛውን እሞክራለሁ” እ— አትበሉ።

28 አንደኛውን እቀበላለሁ። እግዚአብሔር፡ ለአንደኛው ቃል ገብቶልኛል፡ ያንንም ነው የምፈልገው። ላገለገልኩባቸው ለእነዚህ ሃያ-ሦስት ዓመታት፡ ያንን ሰፍራ ሰጥቶኛል። እኔም... እርሱን እስከማምንና እስከምወደው ድረስ፡ እርሱም እስኪወደኝ ድረስ፡ እንዲሁ ይሆናል ምክንያቱም ለቃሉ የታመነ ነውና። “የምትፈልጉትን ሁሉ፡ ስትጸልዩ፡ እንደተቀበላችሁ እመኑ፡ ታገኙማላችሁ።” ያለው ያንን ነው። ልክ ነው? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] ጥሩ ነው። መልካም።

29 “አሜን፡” ስትሉ መስማት ደስ ይለኛል። ታውቂያለሽ፡ እህት ሁቨር፡ ለእኔ፡ **አሜን** ማለት “እንዲሁ ይሁን” ማለት ነው፡ ታውቂያለሽ። ደግሞ እ—እ መናገር ስጀምር፡ ማንም “አሜን” ሲል ካልሰማሁ፡ ግራ ይገባኛል።

30 ከተወሰነ ጊዜ በፊት በትንሽ ቤተክርስቲያን ውስጥ እየሰበክሁ ነበር፡ እ—እኔም ዝም ብዬ... ኦህ፡ የዘመኑን ሥነ መለኮት መሠረት በማድረግ፡ ብዙ የመድረክ ስርዓት እያያዝ እንዳልነበረኝ፡ አገምታለሁ፡ ሰለዚህ እንደሚመስለኝም፡ ትንሽ ሥርዓት አልባ ሆኜ ነበር። ወደ መድረኩ ዘልዬ

የወጣሁ ይመስለኛል-... ወደ ፑልቢት፡ **በዚያ** መንገድ፡ ማይክሮፎኑንም በእጄ ጨብጬ፡ እግሮቼን እያወዛወዝኩ፡ እዚያ ላይ ተቀምጬ፡ በቻልኩት መጠን አጥብቄ እሰብክ ነበር። ወደ ራሴ ስመለስ፥ ምን እያደረግሁ እንደነበረ አላውቅም። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ እንደገና ጠፋሁ፡ ሱሪዬንም እየጠቀለልኩ፡ በመተላለፊያው መካከል ራሴን አገኘሁት። ለምን እንደሆነ አላውቅም፡ ዳሩ ግን በእውነት... ለተወሰነ ጊዜ እዚያ መቆየት ፈለግሁ። መናገር የምፈልገው አንድ ነገር ነበር። በእርግጠኛነት እራሴን ያስደሰትኩበት ቦታ ነበር። ከዚያ በኋላ ለበርካታ ቀናት ያንን እየኖርኩት ቀጠልኩ።

31 አንድ ሰው ወደ እኔ መጥቶ፡ "ስማ፡" አለ፡ አክሎም፡ "እነዚያ ሁሉ ሰዎች፡ 'አሜን' እያሉ፡ እንዴት ልትሰብክ ትችላለህ? "

እኔም፡ "እሱ ነው እንድሰብክ የሚያደርገኝ" አልኩት። አዎ።

32 ድሮ የቆየ ውሻ ነበረኝ። ራኩን አድን ነበር። እዚህ ራኩን ማደን የሚወዱ የኬንታኪ ጓደኞች በብዛት ያሉኝ ይመስለኛል። ስለዚህ... እርሱ ማንኛውንም ነገር ወደ ዛፍ ላይ ያወጣል፡ ሄዶም ያመጣቸው ነበር፡ ከስካንክ በስተቀር፥ እሱን ፈጽሞ አይነካውም። አሁን፡ ከቁጥቋጦ ክምር ሥር ያባርረዋል። እኔም ማድረግ ያለብኝ፡ ከእሱ በኋላ ወደዚያ መግባት እያስፈልግም፡ እርግጠኛ ነበርኩ። ስለዚህ የማደርገው ብቸኛው ነገር፡ ቊጥቋጦውን ብቻ አንሰቼ፡ መታ መታ እያረግኩ፡ "ያዘው፡ ጀግናው! ያዘው!" ብዬ መጮህ ነበር።" እርሱም ሄዶ ስካንኩን ይይዘው ነበር።

33 አሁን እኔ የማውቀው በጣም የከፋ ስካንክ ሰይጣን ነው። ጥቂት መታ መታ ማድረግም ከፈለጋችሁ፡ አልፎ አልፎ "አሜን" ብላችሁ ብቻ ጩሁ። እኔ—እኔም... ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ዛፍ ላይ እናሰወጣዋለን፡ ሄደንም እንይዘዋለን። አያችሁ?

34 ታውቃላችሁ፡ አዛውንቱ በዲ ሮቢንሰን፡ ብዙዎቻችሁ ስለ እርሱ ሰምታችኋል። አይደል እንዴ? የናዝሪን ቤተክርስቲያን። እርሱም፡ "ጌታ ሆይ፡" አለ፡ "እንደ መጋዝ ግንድ ያለ የጀርባ አጥንት ስጠኝ። በነፍሴ ጣሪያ ላይ ብዙ እውቀትን ስጠኝ። አንዲት ጥርስ ብትቀረኝም ከሰይጣን ጋር እንድዋጋ ፍቀድልኝ፡ ከዚያም እስክሞት ድረስ በድዴ እንድታገለው አድርገኝ።" ያ ጥሩ ይመስለኛል... እሱም ያደረገው ያንኑ ነው። ያደረገው ያንኑ ነው፥ ያኔ፡ ወደ መቶ ዓመት ገደማ ሲሆነውም፡ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።

35 እነዚያ የቀድሞ አገልጋዮች እንደዚያ ሲሰብኩ ሰምቻለሁ። ከሰሞኑ፡ ሬዲዮኑን ስከፍት፡ ሞርደካይ ኤፍ. ሃም የተባለ፡ አንድ አዛውንት ወንድም፡ በመቶ ዓመቱ አካባቢ፡ አሁንም ወንጌልን ሲሰብክ ነበር። እኔም፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ ባርከው፡ ወደዚያ ሲደርስም በዘውዱ ውስጥ ከዋክብት ይኑሩት" አልኩ። ወንድም ሃምን፡ በደንብ አላውቀውም። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ወደዚያኛው ምድር ከመሻገሩ በፊት ላገኘው እፈልጋለሁ። ስለዚህም፡ ደግሞ፡ በዚያ ከሚገኙት ብዙ ሰዎች ጋር እጅ ለእጅ ሊጨባበጥ ይችላል። ወደዚያ ሲደርስ የሚጨባበጣቸው ብዙዎች እንደሚኖሩት አውቃለሁ፡ ኦህ፡ ምክንያቱም የቀድሞ አገልጋይ ነበርና።

36 አሁን ጌታ ይባርካችሁ። አሁን ደግሞ፡ ወደዚህ ቃል ከመግባታችን በፊት፡ ደራሲው ወደ ታች ወርዶ እንዲገልጥልን እንጠይቀው።

37 ደጉ የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ቅዱስ ስሙን ለመጥራት፡ ብቁ አለመሆናችንን፡ ኃጢአታችንን፡ እየተናዘዝን፥ በዚያ በተወዳጁና በታላቁ ልጅህ፡ በኢየሱስ ስም ወደ አንተ እንቀርባለን። ምክንያቱም በ... በሰማይ ያለው ቤተሰብ ሁሉ "በኢየሱስ" ስም ተሰይሟል። በምድርም ያለው ቤተሰብ ሁሉ "በኢየሱስ" ስም ተሰይሟል። በዚያም ስም ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፡ ኃጢአተኞችም ሆኑ ቅዱሳን፡ ምላስም ሁሉ ለእርሱ ይናዘዛል። እንግዲያው፡ በሰሙ ስንናገር፡ በአክብሮት፡ በልባችን ውስጥ፡ ምን ያህል ልንነቀነቅ ይገባናል። ስለዚህ በአክብሮት፡ በሰሙ እንጠይቃለን፡ ዛሬ ማታ ወደ እኛ እንድትመጣ፡ ጌታ ሆይ።

38 በዚህች በታላቅ ከተማ መካከል ነን፡ ሰይጣን ሰዎችን በጣም ባሰረባቸው በሁሉም ዓይነት ዘዴዎች፡ በንግዳቸው፡ በቁማሩ፡ በዝሙት፡ በውስኪ፡ በሲጋራም። አምላክ ሆይ፡ ብዙ መጋቢዎችም፡ በመድረኩ ላይ፡ ልክ እንደ አንዱ ተራ ነገር፡ እንዲሁ እንዲያልፍ ያደርጉታል።

39 ነገር ግን፡ አምላክ ሆይ፡ ወንጌልን ቀጥ አድርገንና በእውነት እንድንሰብክ፡ መጥረቢያውንም፡ በዛፉ ሥር እንድናስቀምጥ፡ ፍንካቾቹም በፈለጉት ቦታ እንዲወድቁ የማስጠንቀቂያ ድምጽ ሰጠን። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ በእንደዚህ ዓይነት ነገሮች ላይ ፍርድን እንድናውጅ፡ የተወደደውን የልጅህን የኢየሱስን ወንጌልም፡ እንድንሰብክ እርዳን።

40 አምላክ ሆይ፡ ይህችን ከተማ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያናውጥ ነገር እንዲከሰት አድርግ። እንዲሁም፡ በጥቂት አባላት፡ ማዕዘን ላይ የሚጓዙት፡ አብያተ ክርስቲያናት፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ዳግመኛ በተወለዱ፡ ቅዱሳን በሆኑ፡ የጥንቱን-በሚናፍቁ፡ ይሞሉና ይትረፍረፉ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። የጥንቱን-አይነት፡ ከእግዚአብሔር-የተላከውን ሪቫይቫል፡ እንድንቀበል ይህም ከከተማይቱ አንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ጥግ ድረስ የሚያናውጥ፡ ክፋትን ሁሉ የሚያሰወግድ አድርግልን። እግዚአብሔር ሆይ፡ የሚጓተት ሰብሰባን አትሰጠን። ህገወጥ የመጠጥ ቤቶችን የሚዘጋ፡ ነገሮችን የሚያስተካክል፥ የቤተክርስቲያኑ ደወል ሲደወል፡ ሰዎችን የሚያመጣና፡ ወደ መሠዊያው የሚጎርፉበትንና ከፓስተሩ መልእክት በፊት የሚጸልዩበትን፡ የሚዘጋጁበትን ሪቫይቫል ሰጠን። አምላክ ሆይ፡ ይሁንልን።

41 አሁንም፡ ዛሬ ምሽት፡ እዚህ የታመሙ ሊኖሩ ይችላሉ፡ አባት ሆይ። ስለ በሽተኞች ስንናገር፡ ወይም ለበሽተኞችም፡ ጭምር፡ መንፈስ ቅዱስ በሕንጻው ውስጥ ያለውን በሽተኛ ሁሉ ይፈውስ። ኃጢአተኛውንም ሁሉ ያድን። ኰብላይን ሁሉ፡ ከአመፀኛ መንገዱ፡ ወደ ቤቱ ይመልሰው።

42 አሁንም፡ ዛሬ ምሽት ወደዚህ ርዕሰ የመራኝ መንፈስ ቅዱስ ይሁን። እርሱም የእግዚአብሔርን ነገሮች ይውሰድና ይህን አገልጋዩን እንደ መሣሪያ ብቻ ይጠቀምበት፡ እግዚአብሔርም ክብርን ይቀበል። በሰሙ እንጠይቃለንና። አሜን።

43 በዘኁልቁ፡ ምዕራፍ 20 ከቁጥር 7 ላይ—ይህንን እናነባለን።

**ጌታም ሙሴን፡ እንዲህ ብሎ ተናገረው፡**

**በትሩን ውሰድ፡ አንተና፡ ወንድምህ አሮንም፡ ማኅበሩን ሰብስቡ፡... በዓይኖቻቸው ፊት ዓለቱን ተናገሩት፥ እርሱም የራሱን ውኃ** ይሰጣል፡...

44 ይህን “የራሱን” ውኃ የሚለውን፡ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ።

**... እርሱም የራሱን ውኃ** ይሰጣል፡ **አንተም ከዓለቱ ውኃን ታወጣላቸዋለህ፥ አንተም ለማኅበሩና ለእንስሶቻቸውም መጠጥን ትሰጣለህ።**

**ሙሴም እንዳዘዘው፡ በትሩን ከጌታ ፊት ወሰደ።**

**ሙሴና አሮንም ማኅበሩን በዓለቱ ፊት ሰበሰቡ፡ እርሱም እንዲህ አላቸው፡ እናንተ ዓመፀኞች፡ ስሙ... በውኑ ከዚህ ዓለት ውኃ እናወጣላችኋለን?**

**ሙሴም እጁን አነሣ፡ ዓለቱንም በበትሩ ሁለት ጊዜ መታው፥** ውኃም **በብዙ ወጣ፡ ማኅበሩና፡ እንስሶቻቸውም ጠጡ።**

45 ወደ ትናንት ምሽቱ ርዕሳችን ተመልሰን ወደዚህ ሰናመጣው፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን፡ ጌታ እነዚህን ጥቂት ቃላት አሁን ይውሰዳቸው።

46 አሁንም፡ ዛሬ ምሽት የምፈልገው፡ እዚህ ያላችሁ በሽተኞች ሁሉ... አሁንም፡ ቢሊ ዛሬ ምንም የጸሎት ካርዶችን አልሰጠም፡ ምክንያቱም እንዳይሰጥ ስለነገርኩት ነው። እንዲህ አልኩት፡ “ቢሊ፡ ዝም ብለህ ሂድና፡ ወንድም ካውብልን ንገረው። ደግሞም ለእኔ... ”

47 ለእግዚአብሔር ክብር ስል፡ አንድ ነገር እየሞከርኩ ነው። እግዚአብሔር እንዲረዳን፡ ወደ መንግሥቱ ነፍሳትን እንዲሰጠን ብቻ እየጠየቅኩ ነው፥ እምነታቸውንም የሚያጠነክሩ አማኞችም፡ ያለ ምንም ሌላ ነገር፡ ዝም ብለው፡ ወደ ፊት በመቀጠል፡ “አምላክ ሆይ፡ በቃሉ፡ አምንሃለሁ” እንዲሉ። ያ ነው እንግዲህ። የመጀመሪያውና፡ የቀድሞውም፡ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ያ ነው። ትክክል ነው። እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ እመኑት። ከዚያም፡ ያን ማድረግ ካልቻላችሁ፡ ታዲያ፡ በርግጥ፡ እግዚአብሔር ሌላ ነገር፡ ማለትም ለእያንዳንዱ አማኝ፡ ቃሉን ለ—ለማጽናት፡ እንደ ስጦታዎችና ምልክቶች ይልካል።

እንግዲህ፡ እሁድ ዕለት፡ “መዋጀት በደሙ” የሚል ርዕስ፡ አይተናል።

48 አሁን እስራኤልን፡ በጉዟቸው እንመለከታቸዋለን፡ ከግብፅ ወጥተው፡ ወደ ፍልስጤም፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲሄዱ፡ የዓለም ምሳሌ ናቸው። ይህ የሚያምር ነገር ይመስለኛል። በጣም እወደዋለሁ። በየሳምንቱ ማለት ይቻላል፡ ከቻልኩ ያን የዘጸአት መጽሐፍ ተቀምጬ አነባለሁ፡ ወይም፡ የምችለውን ያህል። እወደዋለሁ ምክንያቱም ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም ምሳሌ ነውና፡ ሁኔታውም፡ እግዚአብሔር እንዴት እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ። ያኔ ተንቀሳቀሰ፡ ያኔ በተፈጥሮአዊው ያደረገውን፡ አሁን በመንፈሳዊው እያደረገው ነው። አያችሁት?

49 አሁንም፡ ያኔ እስራኤልን መራቸው፡ በተፈጥሮአዊው፡ ባዩበት፡ በተመለከቱበት፡ ከአንድ ምድር ወደ ሌላ ተፈጥሮአዊ ምድር አወጣቸው።

50 አሁን እኛ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራን፡ አሁን ወደ ተስፋይቱ ምድር እየሄድን ነው። ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚወስደው መንገድ ላይ እንዳለን ታምናላችሁ? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] “በአባቴ ቤት ብዙ

መኖሪያ አለ። ባይሆንስ፡ ባልኋችሁ ነበር። ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ።” ልክ ነው አይደል? [“አሜን።”] አሁን የምንሄድባት ተስፋ የተገባች ምድር አለችን፡ እያንዳንዱም ቀን የአንድ ምዕራፍ ምልክት ነው፥ ሌላ ቀን፡ የሌላ ምዕራፍ ምልክት ነው።

51 ሞት የሚባል፡ በፊታችን የተቀመጠ አንድ ትልቅ ጨለማ ጥላ አለ። ልባችንም በሚመታበት እያንዳንዱ ጊዜ፡ ወደዚያ አንድ እርምጃ እንቀርባለን። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ የመጨረሻ ምቱን ይመታል፡ እኛም እንገባበታለን። ጊዜዬ ሲደርስ፡ ዛሬ ምሽት፥ ሁላችሁ እንዲሁ መሆናችሁ ተስፋ እንደማደርገው፡ ዕጣዬን እነሣለሁ። በፊቴ ተጋድሞ እንዳለ እያወቅኩ፡ መጋፈጥም ሲኖርብኝ፡ ፈሪ መሆን አልፈልግም። በእርሱ የጽድቅ ልብስ ልጠቀለል እፈልጋለሁ፡ ወደዚያም እየገባሁ፡ ይህን እያወቅኩ፡ እርሱን በትንሣኤው ኃይል እንደማውቀው እርግጠኛ ነኝና። ትክክል ነው። ይህም፡ እርሱ ከሙታን መካከል ሲጠራ፡ ከሕያዋን ጋር አብሬ እጠራለሁ። እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው።

52 አሁን፡ በዚህች ምድር ላይ ጉዞ ላይ ሳሉ፡ እግዚአብሔር ዕቅድ––እንዳዘጋጀላቸው ተረድተናል። እርሱ በደም የሆነ መዋጀትን፡ አስተዋወቀ። ከዚያም፡ እርሱ እንደገና፡ በኃይል የሆነ መዋጀትን፡ እንዳመጣ ተረድተናል።

53 ከትናንት ወዲያ ምሽት፡ ደሙ ተረጭቶ እንደነበር፡ አይተናል፥ ይህም ለአማኙ በጣም የሚያምር ምሳሌ ነበር፡ ያም፡ በአማኙ ምትክ የክርስቶስን ሞት ሲቀበል፡ ያኔ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል። ጉዞውንም ይጀምራል።

54 አሁን፡ ሊኖረው የሚገባው ቀጣዩ ነገር… በመንፈሳዊ፡ ከዳነ በኋላ ነው።

55 አሁን፡ የንጹሑ በግ ሞት ለበደለኛው አማኝ ሕይወትን ሰጠ። አሁን ያ ፍጹም ምሳሌ አይደለምን? የንጹሑ ሞት፡ ለበደለኛው ሕይወትን መስጠቱ። የንጹሑ የክርስቶስ ሞት ደግሞ ለእኛ ለበደለኞቹ ሕይወትን ይሰጣል።

56 አሁን፡ በመጀመሪያ፡ ከዚያም፡ እግዚአብሔር በደሙ ሕይወትን ከሰጣቸው በኋላ፡ ሞት እንዳለፋቸው፡ እንዳረጋገጠውም፡ ጉዟቸው አስጀመራቸው። ከአፍታ በኋላ እናየዋለን።

57 አሁን አስተውሉ፡ ከዚያም፡ እግዚአብሔር ያደረገው ቀጣዩ ነገር፡ አማኞችና ልጆች እንደሆኑና፡ እግዚአብሔርንም እንደተቀበሉ፡ የስጋን ሞት የሚጠላው ተከተላቸው። በአንድ በኩል፥ በረሃው፡ በሌላ በኩል የቀይ ባሕር፥ በሌላ በኩል ተራሮች እያሉ፥ አጣብቂኝ ውስጥ ከተታቸው፥ የፈርዖን ሠራዊት እየመጣ፡ እያሳደደም፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወታደሮች በሰልፍ ድል ሊነሷቸው፡ እየገሰገሱ ነበር።

58 አሁን፡ እግዚአብሔር በበጉ ሞት በኩል፡ ሕይወትን እንደሰጣቸው በግልጽ አሳይቷል፥ አሁን ደግሞ አካላዊ መዋጀትን ሊያሳያቸው ነው። ሃሌሉያ! እያችሁ፡ ለድነትም ለፈውስም፡ እያችሁ፡ ለተፈጥሮአዊው ሰውና ለመንፈሳዊው ሰው።

59 የሞት መልአክ አለፈ፡ እግዚአብሔር በደም መሥዋዕት በኩል፡ የማምለጫ መንገድ እንዳዘጋጀ በማረጋገጥ አለፈ፡ እነርሱም ተቀበሉት። አሁን እርሱ ከአካላዊ ሞት የማምለጫ መንገድን ሊያዘጋጅ ነው።

60 ልክ እንደ አማኙ፡ እንደዳነ። ምናልባት ካንሰር በልቶት ይሆናል፡ ወይም የሆነ በሽታ። እግዚአብሔር በኃይል በኩል፡ ደግሞ፡ መዋጀት አለው። ለነፍስ መዋጀት እንዳለው ሁሉ፡ ለሥጋም መዋጀት አለው። ያ...

61 ድነው ነበር፡ ተገርዘውም ነበር። በደሙ ሥር ነበሩ፡ ነገር ግን፡ ሆኖም፡ ፈርዖን ሊያ... ጠላት ሊያጠፋቸው፡ እዚያው በምድረ በዳ ሊገድላቸውም ነበር፡ ከዚያም እግዚአብሔር ለሥጋቸው የቤዛነት ኃይሉን አሳያቸው። ገባችሁ? የምናገረውን ታውቃላችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] በኃይል የሆነ ቤዛነት! ከዚያም፡ ጠላት ልክ ሊደርስባቸው ሲል፡ ታላቁ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ የእሳት ዓምድ ከእስራኤል በላይ ተነሳ፡ ወደዚህም መጥቶ በእነርሱና በሞት መካከል ቆመ።

62 ለጥቂት ደቂቃዎች እንዲሰርጽባችሁ አድርጉ። የምናገረውን አያችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።]

63 አሁንም፡ ለእያንዳንዱ አማኝ፡ዳግም-ለተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ሞት ሳይታሰብ ወደ ደጃፍ፡ በድንገት ሲመጣ፡ የእግዚአብሔር መልአክ በእናንተና በበሽታው መካከል ይቆማል። አሁን፡ ወደዚያው መሮጥ ከፈለጋችሁ፡ ያ የእናንተ ፋንታ ነው፥ ነገር ግን መሮጥ የለባችሁም። አያችሁ? እርሱ በእናንተና በሞት መካከል ቆሟል።

64 ከሃያ-ሦስት ዓመታት በፊት፡ በአይሁድ ሆስፒታል፡ ዶክተር ሞሪሰ ፍሌቸር ሦስት ሰዓታት ሰጠኝ፥ እዚህ ከተማ ካሉ ምርጥ ቀዶ ጥገና ሐኪሞች አንዱ፡ በህይወት እንድኖር ሦስት ሰዓታት ሰጠኝ። ዛሬ ምሽት ግን፡ በሕይወት አለሁ። ሃሌሉያ! ለምን? ባልተገባኝ ጸጋ፡ የእግዚአብሔር መልአክ እኔን ለመጠበቅ፡ በእኔና በሞት መካከል ቆመ፡ እኔም ተቀበልኩት። በምስጋናም፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፡ ዛሬ ምሽት፡ ግማሽ ሚሊዮን ነፍሳትን ለእርሱ አሸንፌአለሁ።

65 ኦህ፡ እኛ ብቻ ከተከተልን፡ እግዚአብሔር ነገሮችን እንዴት ማድረግ እንዳለበት ያውቃል። እግዚአብሔርን ለመምራት አትሞክሩ። እግዚአብሔር እንዲመራችሁ ፍቀዱ። አያችሁ? መመራት ያለብን እኛ ነን። እግዚአብሔር እኛን በበጎች የመሰለን ለዚህ ይመስለኛል።

66 የጠፋ በግ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ለምን፡ እርሱ በዓለም ላይ በጣም ምስኪን ፍጥረት ነው። መንገዱን የትም ሊያገኝ አይችልም። ተኩላው እስኪበላው፡ ወይም እዚያው እስኪሞት ድረስ ዝም ብሎ ይጮኻል። መንገዱን መልሶ ሊያገኝ አይችልም።

67 ሰውም ሲጠፋ፡ እንደዚሁ ነው፡ ማለትም፡ ሙሉ በሙሉ ረዳት የሌለው ነው። ስለ እሱ ልታደርጉለት የምትችሉት ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር፡ በጸጋው፡ ወደ ክርስቶስ ሊመራችሁ ይገባል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "አብ ካልሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። እርሱ የሚሰባቸውንና፡ የሚመጣውንም ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወትን እሰጠዋለሁ።" ምን ዓይነት ተስፋ ነው!

68 ኦህ፡ እዚህ ያለ እያንዳንዱ ሰው፡ በልብ ዋና ክፍል ውስጥ እስኪነካ ድረስ፡ በግራ በኩል ካለው ከአምስተኛው ጎድን በታች ጠልቆ ቢገባልኝ እመኛለሁ። ሰዎች ሁሉንም ዓይነት በሽታዎች እያለባቸው፡ እንዲሁ ዝም ብለው እየተነሱ፡ በደስታ እየዘለሉ፡ በሽታውን አንቀበልም በማለት፡ ከዚህ ህንጻ ሲወጡ ታዩ

ነበር። ሽባዎችም ልክ እንደማንኛውም ሰው በተለመደው ሁኔታ ይራመዱ ነበር። ሌላ ምንም ነገር ማወቅን እምቢ ይሉ ነበር። አያችሁ?

69 እናንተ ፈርታችኋል። የመጀመሪያውን እርምጃ ለማድረግ ትፈራላችሁ። እግዚአብሔር ወርዶ እንዲጎትታችሁና እንዲያወጣችሁ እየጠበቃችሁ ነው። እግዚአብሔር በዚያ መንገድ አያደርገውም። እርምጃውን መውሰድ ያለባችሁ እናንተ ናችሁ። እርሱ ተሰፋውን ይሰጣል፡ “ኑ” ይላል፡ ከዚያም፡ እናንተ ትከተላላችሁ።

70 አሁንም የእስራኤልን ልጆች አስተውሉ፡ እንግዲህ። እግዚአብሔር መጥቶ በእነርሱና በአደጋው መካከል ቆመ፥ የቤዛነት ኃይል... ማለቴ፡ በኃይል የሆነ ቤዛነት። በደም የሆነ ቤዛነት፥ በኃይል የሆነ ቤዛነት።

71 ትላንት ምሽት፡ በባሕሩ ማዶ ዳርቻ ላይ እየወጡ፡ ትተናቸው ነበር። የጠላቶች ሁሉ፡ የሰረገላ መንኰራኩሮች ተነቃቅለው ነበር። ፈረሶቻቸውም በወንዙ መካከል፡ ደንግጠው ነበር፡ ወደዚህም ወደዚያም እየዞሩ ነበር፡ **ወዲህም** ይሄዱ ነበር፡ መንኰራኩሮቹም በጭቃው ውስጥ ተቀብረው ወላልቀው ነበር። የጠላት ህዝብም፡ በፍርሃት ይሮጥ ነበር። እስራኤልም እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ ጠላትን ሁሉ ሲያጠፋ ለማየት፡ ወደ ዳርቻው ወጡ።

72 የሚያምር ምሳሌ፡ አማኙ፡ በደሙ ሥር፥ መካከለኛ-ሆኖ በገባው ኃይል ተፈውሷል፡ የእግዚአብሔር ኃይል ሕይወቱን ታድጓል፡ ለተወሰነ ጊዜም አራዝሞለታል። እግዚአብሔር፡ በመካከላቸው፡ ባይቆም ኖሮ፥ እዚያው ምድረ በዳ ውስጥ እያንዳንዳቸው ይገድላቸው ነበር፡ ይጨፈጭፋቸውም ነበር። እግዚአብሔር፡ በእኔና በሞት መካከል ባይቆም ኖሮ፡ ከረጅም ጊዜ በፊት እሞት ነበር። እግዚአብሔር፡ በእናንተና በሞት መካከል ባይቆም ኖሮ፡ እዚህ ያላችሁ እያንዳንዳችሁ፥ ከረጅም ጊዜ በፊት ትሞቱ ነበር። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ በሉዓላዊ ጸጋውና ምሕረቱ፡ በአማኙና በሞት መካከል ይቆማል። ሃሌሉያ!

73 ይኸውላችሁ። ከዚያ ለአማኙ ቀጣዩ ነገር ምንድነው? ቀጣዩ ነገር መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ሙሴ የእስራኤልን ልጆች በቀጥታ ወደ ቀይ ባሕር መራቸው፡ በባሕሩም ውስጥ ተጠመቁ። ባሕሩ፡ ውኃው፡ መንፈስን ያመለክታል። ዓለቱን በመታው ጊዜ፡ ውኃ ወጣ። ይህም በዮሐንስ 3፥16 ላይ፡ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። “በእርሱ የሚያምን ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ፡ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” ልብ በሉ፡ በምድረ በዳ ላይ፡ ይህ የሚጠፋው ሕዝብ፡ በተመታው ዓለት ዳነ። ዛሬም የሚጠፋው (በኃጢአት የሚጠፋው፡ በበደል የሚጠፋው) ሕዝብ ድኗል ምክንያቱም የተመታው የእግዚአብሔር ልጅ ሰፍራቸውን ስለተካ ነው፥ ውኃው፡ መንፈሱ፡ እየፈሰሰ ነው!

74 ተመልከቱ፡ አሁንም እንድታዩት እፈልጋችኋለሁ፡ በቀይ ባሕር ውስጥ ማለፋቸው፡ መንፈስ ቅዱስን የመቀበል ምሳሌ ነበር። አማኙ፡ ከሞት ወደ ሕይወት ከተመለሰ በኋላ፥ የእግዚአብሔር ኃይል ሥጋውን ፈውሶታል፥ አሁንም እርሱ ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እጩ ነው። አሁንም፡ ከፊቱ፡ የሚጠብቀው ጉዞ አለው፥ ዳሩ ግን፡ ያንን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት፡ የሚያሻግረው ነገር ሊኖረው ይገባል። አሜን። ፍጹም የሆነ የጴንጤቆስጤ ምሳሌ!

75 ልብ በሉ፡ ከባሕሩ ዳርቻ ሲወጡ... እያንዳንዱ አማኝ፡ ወደ ውስጥ ስትገባና ስትድን፡ የኢየሱስን ደም ስትቀበል፡ አሁንም **ይህንኑና ያንኑ** ለመያዝ ትሞክራለህ፡ **ይህንንም ያንን**ም መተው አትችልም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እግዚአብሔር መልካም ነገሮችን ሊያደርግልህ ይችላል፥ ዳሩ ግን ሲጋራህን መተው አትችልም፡ አልፎ አልፎም ከጓደኞችህ ጋር መጠጥ መጠጣት ትቀማምሳለህ። ነገር ግን ማድረግ ያለብህ በቀይ ባሕር በኩል ማለፍ ነው።

76 ወደ ማዶ ሲወጡ (ይኸውላችሁ፡ እንድታዩት እፈልጋችኋለሁ።)፡ ወደ ማዶው ሲወጡ፡ ወደ ዳርቻው ወጥተው ወደ ኋላ ሲመለከቱ፡ ሲደበድቧቸውና አንዳንዶቹንም ሲገድሏቸው የነበሩትን እነዚያን የቀድሞ፡ አሳዳጆቻቸውን አዩ። ልክ እንደ ካንሰር እና ሲጋራ እንደ ትንባሆና ውስኪ ሌላውም ሁሉ፡ ልጆችን እንደሚያሳብድ፡ ወደ ዕብዶች ማቆያና፡ ወደ ሆስፒታሎች እንደሚሰድድ፡ በዓለም ላይም የነርቭ በሽተኞችን ህዝብ እንደሚያመርት ሁሉ። ወደ ኋላ ተመልክተው እነዚያ ነገሮች ሁሉ ሲታገሉ፡ ረዳት አጥተውና፡ በባሕሩ ውስጥ ሲሞቱ ሲያዩ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ስለ ስብሰባው እያወራህ ከሆነ፥ አንድ ታላቅ ስብሰባ ነበራቸው!

77 ሙሴ! ኦህ፡ ይህ በጥልቀት እንዲሰርጽባችሁ አደርጋለሁ። በጣም ጠልቆ እንዲገባ ተሰፋ አደርጋለሁ። ሙሴ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጭ ከኖሩት ነቢያት ሁሉ ታላቁ ነቢይ። ከክርስቶስ ውጭ፡ እግዚአብሔር እንደ ሙሴ ያነጋገረው ሰው፡ አልነበረም። እርሱም እንዲህ አለ፡ “ከእናንተ መካከል መንፈሳዊ፡ ወይም ነቢይ ቢኖር፡ እኔ በራእይ እገለጥለታለሁ፡ ራሴንም አስታውቀዋለሁ። አገልጋዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፥ እኔ ከእርሱ ጋር ፊት ለፊት እናገራለሁ።” ይህ ትክክል ነው።

78 ሙሴ፡ ይህ የተከበረ ሰው። ያንን ተሞክሮ እንዳለፈ ወዲያው፡ እነዚያ አሳዳጆች ሁሉ መሞታቸውን አየ፡ እነዚያ ነገሮች ሁሉ ለዘላለም መወገዳቸውን ያን ጊዜ አወቀ። ሲያባርሯቸው፡ ሲደበድቧቸውና፡ ሲገረፏቸው የነበሩት ነገሮች ሁሉ፡ ተጠናቀቁ። እጆቹን አንስቶ በመንፈስ ዘመረ። ኦህ፡ ማይ!

79 የቀድሞ፡ ምሳሌ ተደርጎ አያውቅም፡ ወደ ሰማይ ክብር እስከምንደርስ ድረስም አይሆንም። ፍጻሜው በዚያ ሲደረግ፡ እርሱ በመንፈስ ዘመረ። እኛም በሥጋ ሰንዋጅ...

80 ያ በጴንጤቆስጤ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ የሚያሳይ ምሳሌ ነበር፡ በባሕሩ ውስጥ ስናልፍ። የጴንጤቆስጤ ምሳሌ ነበር። ሙሴም፡ በዚያ በ-... በዚያ በቀድሞ ምሳሌ ውስጥ፡ በዚያ ውስጥ ሲያልፍ፡ በመንፈስ ዘመረ። በጴንጤቆስጤ ቀን መጣ። ሥጋችንም ፍጹም ሆና፡ ስትቤዥ... አሁን ነፍሳችን ፍጹም ሆና ተቤዥታለች፡ ትክክል ነው፡ “አትጠፋም፥ የዘላለም ሕይወት አላት።” መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ይህንን ነው!

81 ኦህ፡ ደስ ይለኛል። ለምን እንደሆነ ልብ በሉ። ምክንያቱም **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** መሆኑን አውቃለሁ። ነፍሴን በዚያ አስሬ፡ እየተጓዝኩ፡ እንዲህ እላለሁ፡ “ሰይጣን፡ የፈለግከውን ያህል፡ በእኔ ላይ ተቆጣ። አይረብሸኝም፡ ምክንያቱም ያመንኩትን አውቃለሁና፡ ለዚያ ቀን የሰጠሁትንም እርሱ ሊጠብቀው እንደሚችል እርግጠኛ ነኝ።” አሜን።

82 ዛሬ ምሽት እዚህ በሉዊስቪል ዙሪያ፡ እኛ የሚያስፈልገን፡ የድሮው-ዓይነት፡ ቢሊ ሰንደይ፡ ትሁት-የሆነ፡ የሃሌሉያ ሪቫይቫል ነው። ይህ ትክክል ነው፡ ጥሩ የሆነ፡ የድሮ-ዓይነት፡ እግዚአብሔር-የላከው የጴንጤቆስጤ ሪቫይቫል ያስፈልገናል። አዎ፡ ወዳጄ።

83 እንግዲህ፡ ልብ በሉ፡ ሥጋችን ሲቤዥ... ይህ አሁን፡ እንደ ጥላ፡ መለኮታዊ ፈውስ አለን።

84 ያ የጴንጤቆስጤ ጥላ እንደነበረው ሁሉ፡ በዚያ በመዳን ጥላ ጊዜ ያደረጉትን፡ ተመልከቱ። በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንደተጓዙ ተመልከቱ፡ "የእሳትን... ኃይል... አጠፉ፡ ከሰይፍም አፍ አመለጡ፡" እነዚህን ሁሉ ነገሮች አደረጉ፡ "ከሚነድድ የእሳት እቶን ወጡ፥ ከአንበሶች ጉድጓድና፡ ከሁሉም፡" በጥላው በኩል፡ ሃሌሉያ፡ በጴንጤቆስጤ ጥላ በኩል ተረፉ።

85 አሁንም በክርስቶስ ደም ፍጹም ቤዛነት አለን። ያን ጊዜ ፍጹም ቤዛነት ሊኖራቸው አልቻለም፡ ምክንያቱም በሬዎችና በፍየሎች ደም ሥር ስለነበር፡ ኃጢአትንም አያስወግድም ነበር፥ ኃጢአትን ይሸፍን ብቻ ነበርና። ዳሩ ግን እጅግ ቅዱስና ጻድቅ ደም፡ የኢየሱስ ደም ሲፈስ ግን፡ ኃጢአት ዳግመኛ አልተሸፈነም፥ ተፋትተው ተለያዩ እንጂ፡ ለአማኙም በፈጣሪው ፊት መግባት ሆነለት። ሃሌሉያ!

86 ያኔ የነበረው ያ ጥላ፡ ሙሴ በመንፈስ ሲዘምር፡ ያን ጊዜ ያንን ካደረጉ፥ እንግዲያውስ፡ በራእይ መጽሐፍ ውስጥ፡ የሥጋ ፍጹም ቤዛነት ያገኙቱ፡ በመስታወት ባሕር ላይ ቆመው፡ የሙሴን ቅኔ በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ደግመው ዘመሩ።

87 ስለ መንፈስ ቅዱስ ስብሰባ—ካላችሁ? በዚያ ዳርቻ ላይ በደረሱ ጊዜ አድርገው ነበር። ስሚ፡ እህቴ። ትንሿ የተከበረችው፡ ነቢይት ሚርያም፡ የሙሴ እህት፡ ነቢይት፡ በጣም ከመደሰቷ የተነሳ ከበሮ ይዛ ወደ ዳርቻው ሮጠች፡ ይህንንም ከበሮ እየመታች፡ በመንፈስ ጨፈረች። ያ ብቻ አይደለም፡ የእስራኤል ሴት ልጆችም ሁሉ፡ በመንፈስ እየጨፈሩ ተከተሏት። መንፈስ ቅዱስ መውረድ ያ ካልሆነ፡ ሌላ አላውቅም። ለምን፡ በእርግጥም፡ እነዚያ፡ አምልኮዎች የሚከተሉ፡ የተከበሩ አሕዛብ በማጉያ መነጽራቸው አይተዋቸው ቢሆን ኖሮ፡ "ወግ አጥባቂነት፡" ይሉ ነበር። በትክክል። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ነበር። በትክክል!

88 ዛሬም፡ የተከበሩት ነገሮች፡ እግዚአብሔር በባረከው ላይ በንቀት ይመለከታሉ። ትክክል!

89 አንድ ታሪክ ያስታውሰኛል። አንድ ሰው ትልቅና ያማረ እርሻ ነበረው። ትልቅና ያማረ በረቶች ገነባ፡ ልክ እንደ ዘመኑ የተሸሞነሞነና ክላሲክ የሆነ ነበር፡ ነገር ግን እርሻውን ለማረስ እጅግ ይለግም ነበር። እሺ። ሌላ ገበሬ ደግሞ በአቅራቢያው ይኖር ነበር፥ እሱ እንደዚያ አይነት በረት አልነበረውም፡ ሆኖም እርሱ እውነተኛ ገበሬ ነበር፡ በዚያ ዓመትም በበረቱ ውስጥ ብዙ ጥሩ ምግብ አከማችቶ ነበር። እናም ሁለት ትናንሽ ጥጃዎች ተወለዱ፡ አንዱ በአንዱ ጎተራ ውስጥ ሌላኛው ደግሞ በዚያኛው ውስጥ። የጸደይ ወቅት ሲመጣ፡ ትንንሾቹን ጥጃዎች ከየበረታቸው አወጧቸው።

90 ያኛው ከዚህኛው ወገን ያለው ትንሽ ጥጃ፡ በደንብ ሲመገብ ከርሟል፡ አቤት፡ ያ ንፋስ ሲነፍስበት ሲጀምር፡ ኦህ፡ ማይ፡ ተረከዙን አነሳና፡ ሄደ፡ በቻለው ፍጥነት ሮጠ፥ እየተንተባተበ፡ እየዘለለ፡ እናም እየፈነጨ፡ ተንቀሳቀሰ።

91 ከዚያም፡ ሌላኛው ገበሬ የእርሱን ወደዚያ አወጣ። እርሱ—እርሱ ከአረም በቀር የሚበላው ምንም አልነበረውም፥ ለማረስ እጅግ ልግመኛ፡ እርሱን ለመመገብ እጅግ ልግመኛ ነበር።

92 ከእነዚህ አንዳንድ ፓስተሮች ጋር ያመሳስለዋል። ትክክል! ትክክል! በጣም ሰነፍ! በጣም ግድ የለሽ ነው። አሁንም ያላችሁ ሁሉ የተከበሩ በረቶች ብቻ ናቸው። እዚያ ውስጥ ለጥጃው ጥቂት ምግብ ያኖራሉ! ትክክል። ትክክል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ በኃይል የተሰበከ ሰብከት፡ ይለበልባቸዋል። ይህ ትክክል ነው። ሆኖም እነርሱ የሚያስፈልጋቸው፡ ቤተክርስቲያን የሚያስፈልጋት፥ አባላቱ የሚያስፈልጋቸው፡ አንዳንድ ጥሩ የድሮ-ዓይነት መለብለብ ነው። ልብ በሉ።

93 አሁንም ይህ ትንሹ ጥጃ ተጎድቶ ነበር። ምስኪኑ፡ ትንሹ ጥጃ ከበረቱ ወጣ፡ በጣም ከመክሳቱ የተነሳ መራመድ እንኳ አልቻለም ነበር። አሁንም በሰንጥቁ ውስጥ፡ አሻግሮ ተመለከተ።

94 አሁንም ያኛው ጥጃ ሲያናፋ አየ። እርሱ በጣም ወፍራም እና የሰባ ነበር። ደስ ብሎት ነበር። ክረምቱን ሙሉ ሲበላ ቆይቷል።

95 አሁንም ያ ትንሽ፡ የራበው ጥጃ አሻግሮ ተመለከተና፡ "ይህ ወግ አጥባቂነት ነው፡" አለ! ወይኔ! አዎን፡ እርሱ ሌላ ነገር ለማሰብ በጣም ከሰቶ ነበር።

96 ዳሩ ግን፡ እነግራችኋለሁ፡ ያ ክረምቱን ሙሉ፡ የሰባው ጥጃ፡ ወንድሜ ሆይ፡ የት እንዳለ ያውቅ ነበር። ያ ሞቃታማ ነፋስ በእርሱ ላይ መፍሰስ ሲጀምር ጥሩ ጊዜ እያሳለፈ ነበር።

97 አሁንም ከእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ ማንኛውም ሰው፡ አክራሪ ወይም ሌላ ነገር ይሉታል። ዳሩ ግን ያ ሞቃታማ፡ የጸደይ፡ የመንፈስ ቅዱስ ነፋስ ልክ በጴንጤቆስጤ ቀን እንደሆነው መምጣት ሲጀምር፡ አንድ ነገር ሊከሰት ነው። ትክክል። ሞቃታማው ነፋስ መፍሰስ ይጀምራል፥ ወንድሜ ሆይ፡ እናንተ በወንጌል የሰባችሁ ናችሁና፡ ሁላችሁም ደስ ይላችኋል። እየዘለላችሁና ደስ እያላችሁ ቦርቁ።

98 ሚርያምና ሌሎቹ ያደረጉት በዚህ መንገድ ነበር። ወደ ኋላ ተመልክተው በአንድ ወቅት ያደረጓቸውን የቀድሞ ነገሮች ሁሉ አዩ፡ ሁሉም ሞተው ተወግደዋል። እግዚአብሔር ደሙን እንደተቀበለ አይተዋል፥ በመካከላቸው የቆመውን፡ የመለኮታዊ ፈውሰ ኃይሉን አይተዋል፥ በቀይ ባሕር በኩል መጥተዋል፡ በመንፈስም ተጠምቀዋል፥ በሌላኛው ወገን ተራምደዋል፡ እንዲሁ ጥሩ ጊዜ አሳልፈዋል። ድርጅት ሁሉ ስለዚህ ጉዳይ... ምን እንደሚያስብ ግድ አልነበራቸውም። አሜን።

99 ዛሬ እርምጃ ለመውሰድ ለሚደፍር አማኝ፡ እንዴት ያለ ፍጹም ምሳሌ ነው!

100 እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚያቀርብላቸው ቃል ገብቷል። እኛም የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሚያቀርብልን ቃል ገብቷል። እርሱም ፈጽሞ፡ "የፈውስ መንገድ አዘጋጃለሁ፥ **የዚህን** መንገድ አዘጋጃለሁ፥ **የዚያን**

መንገድ አዘጋጃለሁ” አላላቸውም። እርሱ ግን፡ “ከእናንተ ጋር እሆናለሁ” አለ! ሃሌሉያ!

101 ለእኛም ያለው ይህንን ነበር። “እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ እንዲያውም በውስጣችሁ።” ልል የምችለው ይህንኑ ብቻ ነው። እንግዲህ **ስለዚህ፡ ስለዚያ፡** ወይም **ስለሌላው** መከራከር የለባችሁም። እርሱ እዚህ ካለ፡ ያ ያረካኛል፥ መለኮታዊ ፈውስ እዚህ አለ፡ ኃይል እዚህ አለ። ያኔ የነበረው ማንኛውም ነገር፡ አሁንም ነው፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።” ስለዚህ፡ ሥነ መለኮታችሁን ይዛችሁ አብራችሁት ልትሰጥሙ ትችላላችሁ። ወንድሜ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ለዘላለምም ያው እንደሆነ እምናለሁ፥ “እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ እንዲያውም በውስጣችሁ፡” ብሏል። አዎ።

102 እናም ከዚያም ወጡ፡ እርሱም ከእነርሱ ጋር ነበረ። አሁን እንዲህ አለ... ኦህ፡ በራሳቸው ላይ የነበረው ቅርጫት እንጀራ፥ ሁሉም ተበልቶ አልቆ ነበር። ምንም አልነበራቸውም። በዚያች ሌሊት፡ ትንሽ ተርበው ተኙ። ነገር ግን በሚቀጥለው ጠዋት ሲነሱ፡ መሬቱ ላይ በሙሉ እንጀራ ተዘርግቶ ነበር።

103 እግዚአብሔር ነገሮችን የሚያደርገው በዚህ መንገድ ነው፥ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ እንድትመጡ ያደርጋችኋል፡ ከዚያም በእርሱ በኩል ምን ሊደረግ እንደሚችል ያሳያችኋል። ልክ ነው። ይህን ማድረግ ይወዳል። ይወደዋል። ህዝቡን ማስገረም ይወዳል።

104 እናንተ ወንዶች ሚስቶቻችሁን እንደዚያ ማድረግ ትወዳላችሁ። ልደቷ እስኪደርስ ትጠብቃላችሁ፡ ስለምትወዷት፡ በጥበቃ ውስጥ ብቻ ታቆዩአታላችሁ።

105 እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እስከ መንገዱ መጨረሻ ድረስ እንድንመጣ የሚፈቅድበት ምክንያት ይህ ነው፡ ምክንያቱም ስለሚወደንና ከተፈጥሮ በላይ የሆነውንና ኃይሉን ማጽናት ስለሚፈልግ ነው። ስለሚወደን፡ የሚያደርግበት ምክንያት ይህ ነው። አዎ። ልክ የመጨረሻውን እርምጃ ለመራመድ ወደተዘጋጀንበት ስፍራ ድረስ እንድንመጣ ይፈቅዳል፡ ከዚያም ወደ ትዕይንቱ ውስጥ ይገባል።

106 ዕብራውያን ልጆች በቀጥታ ወደ እሳቱ እቶን ውስጥ እንዲገቡ ፈቀደ፡ ነገር ግን በዚያ አራተኛ ሰው፡ እሳቱን፡ ከእነርሱ እየከለከለ ቆሞ ነበር። አያችሁ? እርሱ ሁልጊዜ እዚያ አለ። ፈጽሞ አይተወንም። ሁልጊዜ ቅርብ ነው። “የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል።”

107 ያኔ፡ በዚያች ሌሊት፡ በሚቀጥለው ጠዋት ያንን እንጀራ ለቀሙ። ገና በኤርትራ ባሕር በኩል ያለፋትን፥ ገና በደሙ የጸኑትን ተዓምራዊ ኃይል ያዩትን እነዚያን እስራኤላውያን ማየት እያቸዋለሁ፥ የእግዚአብሔርን ፈዋሽ ኃይል፡ ወይም በእግዚአብሔር እና በእስራኤልና... በግብፅ መካከል የቆመውን፥ ጠላቶቻቸውም በዚያ ጀርባ ሰምጠው ነበር።

108 ልክ የቀድሞ ካንሰር ለዘላለም እንደጠፋው፡ ዕውርነቱም ጠፍቷል፡ መስማት አለመቻሉም ጠፍቷል፡ የስኳር ህመሙም ጠፍቷል፡ ሁሉም ነገር በዚያ ማዶ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ውስጥ ሰምጧል። ምን ይሰማችኋል? አቤት!

109 በመንገድ ላይ ስትራመዱ፡ አንዳንድ ነቃፊዎች እንዲህ ሊሉ ይችላሉ፡ “ቆይ እስቲ አንድ ደቂቃ! በዚህ ግን እርግጠኛ ነህን? ”

“እኔን አታናግሩኝ።” አሜን። ኦህ፡ ማይ!

110 እነርሱን እዚያ ውጭ፡ ዝም ብለው ሲሰበሰቡና እየተከማቹ፡ ሲበሉና፡ አስደሳች ጊዜ ሲያሳልፉ ይታዩኛል። ልክ እንደ የጥንቱ-ዓይነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ስብሰባ። የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ አንዲት ታናሽ ቅድስት ላይ ሲመጣ ይታያል፡ እጆቿን ወደ ላይ ትዘረጋለች፥ ልክ በልቧ ውስጥ ትቀበለዋለች፡ ከዚያም “ጌታ ይባረክ፡” ብላ ትጮኻለች! ልክ እንደዚያ ያለ የቀድሞ-ዓይነት ስብሰባ። አዎ፡ ወዳጄ። ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው ይቀባበሉ ነበር፡ መልካም ጊዜም ያሳልፉ ነበር።

111 አሁን፡ ያ እንጀራ ፈጽሞ አላቆመም። በጉዞው ሁሉ፡ አብሯቸው ሄዷል። በትክክል። በእኛም ውስጥ ላለው ጴንጤቆስጤ ፍጹም ምሳሌ ነበረ። ያም በተፈጥሮአዊው ነበረ። ያ እንጀራ ፈጽሞ አልተቋረጠም። ተስፋይቱ ምድር እስኪገቡ ድረስ፡ ያው እንጀራ ሆኖ ቆየ። ልክ ነው? እናንተ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ይህን ታውቃላችሁ። ከዚያም እኛ…

112 ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችው፡ አማኞች በዚያ በላይኛው ክፍል በነበሩበት ጊዜ በጴንጤቆስጤ ቀን ነበረ። “እንደ ኃይለኛ ነፋስ ያለ ድምፅም መጣ፡ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው።” በዚያን ጊዜ የወረደው መንፈስ ቅዱስ፡ አሁንም ይወርዳል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ይወርዳል። እንዲሁ ይቀጥላል። እንጀራችን ነው። በተፈጥሮ እንጀራ ተመግበው ነበር፥ በመንፈሳዊ እንጀራ እንመገባለን።

113 ኢየሱስ፡ “ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረድኩ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡” አለ።

114 እነርሱም፡ “አባቶቻችን በምድረ በዳ፡ ለአርባ ዓመታት ያህል መና በሉ” አሉ።

እርሱም፡ “እነርሱ’ማ፡ ሁሉም፡ ሞተዋል” አላቸው። አዎን፡ ወዳጄ።

115 “ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ግን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፡ በመጨረሻውም ቀን አስነሳዋለሁ። ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረድኩ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ፡ ለዘላለም አይሞትም።” እንግዲህ እንዲህ ነው። እነርሱ ተፈጥሮአዊውን አገኙ፥ እኛ ደግሞ መንፈሳዊውን አገኘን። ኦህ፡ በምንም ነገር አልለውጠውም። ድንቅ ነው!

116 “ኦህ፡” እናንተም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አንተ አክራሪ መሆንህን ሁላችንም እናውቃለን” ትሉ ይሆናል። እንግዲህ፡ እኔም፡ አውቃለሁ። እኔስ ስለ ክርስቶስ ሞኝ ነኝ። አንተስ የማን ሞኝ ነህ? የዲያብሎስ ሞኝ ትሆን ይሆናል። መልካም ነው። ስለዚህ፡ ስለ ክርስቶስ ሞኝ መሆንን እመርጣለሁ፡ አንተስ አትመርጥም ወይ? መልካም።

117 ተመልከቱ፡ ስለዚያ መና ሌላው ነገር ደግሞ ይህ ነው። መቅመስ ሲጀምሩ፡ “ጣዕሙ እንደ ማር ነው፡” አሉ። አዎ፡ ጣፋጭ ነበረ። እነዚያ የቀድሞ፡ ቅዱሳን ከንፈራቸውን እየመጠጡ ሲበሉ ይታዩኛል። ጥሩ ነበረ።

118 **ይህንን** ቀምሳችሁ ታውቃላችሁ? **ይህም** ደግሞ፡ ጥሩ ነው። “እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ፡ ቅመሱና እዩ፡ ይላል። ጣዕሙ በአለት ውስጥ እንዳለ ማር ነው።” ይህንን አስተያየት፡ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ። ያ፡ የጥንቱ ዘመን ዳዊት፡ በመዝሙሩ እንዲህ ብሎ ተናግሯል፡ “ጣዕሙ በአለት ውስጥ እንዳለ ማር ነው፡” ብሏል።

119 ዳዊት፡ እረኛ በመሆኑ፡ በጎናቸው የሚይዙት፡ ትንሽ ኮረጆ ነበረው፡ ሁልጊዜም ማር በውስጡ ይቋጥሩ ነበር። የጥንቱ እረኞች እንዲሁ ያደርጉ ነበር፡ አሁንም፡ በ—በፍልስጤም እንዲህ ያደርጋሉ። የታመሙ በጎቻቸው—መዳከም ሲጀምሩ፡ ወዲያውኑ፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ እጁን ሰደድ አድርጎ ከዚህ ማር ትንሽ ይወስዳል፡ ከዚያም በአለት ላይ፡ በኖራ ድንጋይ ላይ ይቀባላቸዋል። በጎቹም ያንን ማር ይወዱታል፡ ስለዚህ ያንን ማር ከአለቱ ላይ መላስ ይጀምራሉ። በዚያ የኖራ ድንጋይ ውስጥ ደግሞ የታመመውን በግ የሚፈውስ የሆነ ነገር አለ።

120 እላችኋለሁ፡ ዛሬ ሌሊት እዚህ ኮረጆ ሙሉ ማር አለልን፡ በአለቱም ላይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እናደርገዋለን። የታመሙት በጎችም መላስ ሲጀምሩ፡ በእርግጥ ትድናላችሁ። ልክ ነው፡ ዝም ብላችሁ ላሱ፡ ላሱ፡ ላሱ። ማሩን እየላሳችሁ ሳለ፡ እንግዲህ፡ ከኖራ ድንጋዩም የተወሰነ እንደምታገኙ እርግጠኛ ናችሁ። ያ እንደማንኛውም ነገር እርግጠኛ ነው። አሁንም፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ አናደርገውም። በሚገባው ስፍራ ላይ፡ በክርስቶስ ላይ እናደርገዋለን። ልክ ነው። ምክንያቱም፡ ፈውስ የክርስቶስ ነው፡ አሜን፡ ልክ እንደ ሌሎቹ የቤዛነት በረከቶች ዓይነት ነው። ልብ በሉ።

121 ሌላው ደግሞ። ያ መውረድ በጀመረ ጊዜ፡ አሮን ወጥቶ ብዙ የጎሞር መለኪያዎችን እንዲያመጣ ታዝዞ ነበር።

122 እናም፡ ለቀጣይ ቀን ጥቂት ለማስቀረት ቢሞክሩ፡ ይበላሸባቸው ነበር። ዛሬ ምሽት የመንፈስ ቅዱስ በሆኑት ህዝቦች መካከል ያለው ይኸው ነው። እናንተ እንዲህ ለማሰብ ትሞክራላችሁና፡ “አይ፡ ከሃያ ዓመት በፊት፡ ጥሩ መልዕክት ነበረን። ጥሩ ጊዜ ነ—ነበረን።” ቁም ነገሩ ዛሬ ምሽት ምን አላችሁ? ነገሩ ያ ነው። እ...

123 በየምሽቱ ይወርድ ነበር። በሰንበት ቀን—ላይ ብቻ ካልሆነ በቀር፡ አንድም ጊዜ እንኳ አይቋረጥም ነበር። በትክክል። አሁንም እግዚአብሔር በየምሽቱ፡ አዲስ አድርጎ፡ ልኮታል፥ በየቀኑ፡ በየሰዓቱ፡ ይመጣል።

124 ልብ በሉ፡ እነዚያ የጎሞር መለኪያዎች ተጠብቀው ነበር። እንዲህ አለ፡ “አሁንም፡ ተመልከቱ፡ ወደ ምድሪቱ ስትገቡ፡ ልጆቻችሁም ስለዚሁ መጠየቅ ሲጀምሩ... ” አለ፡ “ወደ ክህነት የሚመጣ እያንዳንዱ ካህን፡ ወደ ቅዱሱ ስፍራ ለመግባት ፈቃድ ካገኘ በኋላ፡ ወዘተ፡ እና ተሹሞ፡ ካህን ከሆነ፡ ከዚያም በመጀመሪያ የወረደውን የመጀመሪያውን መና አንድ ጉርሻ የመውሰድ መብት ነበረው።” መጀመሪያ የወረደውን፡ አንስተው በጎሞር መለኪያ ውስጥ አኖሩት፡ ጠበቁትም፡ ለካህናት ብቻ የተጠበቀ ነበር።

125 አሁን እናንተ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ያ ዛሬ ምን ዓይነት ምሳሌ አለው” ትላላችሁ?

126 እንዴታ፡ እኛ ካህናት ነን። “እናንተ የንጉሥ ካህናት፡ ቅዱስ ሕዝብ፡ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፡ መንፈሳዊ መሰዋዕትን ለእግዚ አብሔር የምታቀርቡ፡ የከንፈሮቻችሁ ፍሬም ለሰሙ መሰዋዕትን የምታቀርቡ።” አሜን። ይኸው ነው። አሁን፡ ከዚያ በኋላ፡ በጴንጤቆስጤ ቀን፡ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፥ መናችን።

127 አሁን፡ በዚያ በቀድሞው ኪዳን የነበረ፡ እያንዳንዱ ካህን፡ ካህን ለመሆን በመጣ ጊዜ፡ ከመጀመሪያው መና አንድ ጉርሻ እንደሚያገኝ ያውቃል፥ ተዘጋጅቶ የቀረበ አልነበረም፡ እሱን መሳይ ሰው-ሰራሽ አይደለም። ነገር ግን ከመጀመሪያው ያገኝ ነበር።

128 እንግዲህ፡ በጴንጤቆስጤ ቀን፡ መናችን መውረድ በጀመረ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደሚነጥቅ ብርቱ ነፋስ መጣ። በዚያም በሰገነት ክፍል ውስጥ፡ መቶ ሃያ ያህሉ፡ የተከበሩ ሰዎች፡ ጥቂት ህዝብ ነበሩ፥ በሮች ተዘግተዋል፡ መስኮቶች ወርደዋል፡ እዚያ ተቀምጠው፡ ተስፋውን እየጠበቁ ነበር። አዎን፡ በርግጥም፡ ከኢየሱስ ጋር የነበሩ ነበሩ። ኃይሉ፡ ያንን ሁሉ የሚያውቁ ነበሩ፡ ነገር ግን ተስፋውን ይጠብቁ ነበር።

129 ዛሬ ምሽት የምንፈልገው ያንን ነው። እንግዲህ... ይህ ህዝብ በዚያች ሌሊት እንደነበሩት፡ በአንድ ልብ ቢሆኑ ኖሮ፡ ያው ነገር ዛሬ ምሽትም፡ እዚሁ በዚህ ሕንፃ ውስጥ፡ በሉዊቪል፡ ኬንታኪ፡ በጴንጤቆስጤ ቀን የተፈጸመው ይደገም ነበር። በትክክል። ኡህ፡ በእርግጥ፡ እዚያ እንደነበሩት ዓይነት ተቺዎች እዚህ ሉዊቪል ውስጥም ይኖራሉ። ነገር ግን፡ ሁሉም በአንድ ሰፍራ፡ በአንድ ልብ ነበሩ። እና በድንገት...

130 አንድ ደብዳቤ የያዘ፡ አገልጋይ መጣና፡ ሰማቸውንም ፈረሙና የኅብረት ቀኝ እጃቸውን ሰጥተው፡ ወደ ቤተክርስቲያን ኅብረት ገቡን? ያ ምናልባት ዛሬ ሊሆን ይችላል፡ ያኔ ግን አልነበረም። የፕሮቴስታንት የሚያደርጉት በዚህ መንገድ ነውና። ካቶሊኩም ወደ መሠዊያው ይሄድና የመጀመሪያውን ቁርባን ይቀበላልም፥ ምላሱን ያወጣና፡ ብስኩቱን ይወስዳል፥ ካህኑም ወይኑን ይጠጣል። ከዚያም እርሱ ያንኑ ነገር ይሆናል።

131 ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ “በጴንጤቆስጤ ቀን፡ በአንድ ልብ ሆነው፡ በአንድ ሰፍራ ነበሩ፡ ከዚያም ድንገት ከሰማይ ድምፅ መጣ፡” ምንም ዓይነት የሰው አስተዋጽኦ አልነበረውም፡ “እንደሚገሰግስ ኃይለኛ ነፋስ። ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት ሁሉ ሞላው።” የእግዚአብሔር ኃይል ወረደባቸው! ልክ በቀይ ባሕር በኩል ሲመጡ፡ ያኔ እንዳደረጉት፥ እንደ እብዶች ሆነው ወደ ጎዳና ወጡ። ልክ ነው? ጮኹ። ቀጠሉ። ተንገዳገዱ። በከንፈሮቻቸው ተንተባተቡ።

132 እነሱ፡ ኡህ፡ እንዴት ያለ ግርግር፡ እ... ህዝቡ፡ ድርጅታዊው ቤተ ክርስቲያን፡ ወደ ኋላ ተመልሰው ቆመው፡ “እነዚህ ሰዎች በአዲስ የወይን ጠጅ ሰክረዋል” እስኪሏቸው ድረስ።

133 ሃሌ ሉያ! ለማንኛውም፡ “ሆሊ-ሮለር” ብላችሁ መጥራታችሁ አይቀሬ ነው፡ ስለዚህ አሁኑኑ ብትጀምሩ ይሻላል። መልካም።

134 ተመልከቱ፡ አዲስ የወይን ጠጅ ተሞልተዋል፡ ትክክል ነው፡ ከእግዚአብሔር፡ ከሰማይ የመጣው የወይን ጠጅ። የሰከረ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ? ዝም ብሎ ሁሉንም ሰው ይወዳል፡ አያችሁ። ግድ የለውም። ሰው በመንፈስ ሲሰክርም እንደዚሁ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡

“በወይን ጠጅ አትሰከሩ፡ ይህ ማባከን ነውና፡ ነገር ግን በመንፈስ ተሞሉ።” የእግዚአብሔር መንፈስ በጣም እንድትሰክሩ ያደርጋችኋል፡ ጠላቶቻችሁን ሁሉና፡ ሁሉንም ነገር ያሰረሳችኋል። ሁሉም ሰው ይወዳችኋል። በዙሪያችሁ ማን እንደቆመ ግድ አይሰጠውም። በዚያን ጊዜ በሀገሪቱ ውስጥ ትልቁ ሰው ናችሁ።

135 አጠገባችሁ የተቀመጠው፡ ጎረቤታችሁ፡ ወደሆነ የተከበረ ቤተክርስቲያን ቢሄድ ግድ የለኝም፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ ጊዜ ብቻ ይውረድባችሁ፡ ምን እንደሚሆን ጠብቁ። በትክክል፡ በሚገባ፡ በደንብ ስከሩ፡ ምን እንደሚሆን ታያላችሁ። እናንተም፡ “እህቴ፡ አገኘሁት! እንቺንም፡ ያስፈልግሻል” ትላላችሁ! ልክ ነው። አዎ፡ ወዳጄ፡ አንድ ነገር ይከሰታል።

136 ሁሉም በአዲስ የወይን ጠጅ ሰክረው፡ በዚያ ነበሩ። ደግሞም፡ እዚህ ያላችሁ አንዳንድ እህቶች፡ ይህን ሰሙኝ፡ የተባረከችው ድንግል ማርያም በዚያ እንደነበረች ታውቃላችሁ? እንግዲህ፡ እሷ ወደዚያ መውጣት ተገባት። የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ወደዚያ መውጣትና በዚያ ህዝብ ውስጥ መካተት ተገባት፡ በመንፈስ በጣም ስክራ ስለነበር ልክ በውስኪ ወይም በሌላ ነገር እንደሰከረች ተወላገደለች።

137 እናንተ ደግሞ ወደ ቤተክርስቲያን ሾልካችሁ በመግባት የመዝሙር መጽሐፋችሁን በብብታችሁ ስር በመያዝ፡ እና በየእሁድ ጠዋት በእግር በመሄድ፡ ደወሉም ሲደወል፡ ተቀምጣችሁ የተወሰነውን... በመሰማትና ተመልሳችሁ በመሄድ መንግስተ ሰማያት የምትገቡ ይመስላችኋል? ፈጽሞ አይሳካላችሁም።

138 በዚያ መንገድ መምጣት ይኖርባችኋል፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ያስቀመጠውና ያለው ብቸኛው መንገድ፡ እሱ ብቻ ነው። በእሱም ትሄዳላችሁ፡ አለበለዚያ እዚያ አትገኙም። ፈራጃችሁ አይደለሁም፡ ነገር ግን ወንጌልን እየሰበክሁ ነው። ይህ በትክክል እውነት ነው። ብጽዕት ድንግል እዚያው ነበረች፡ ልክ እንደሌሎቹ በሞኝነት፡ ልክ እንደሌሎቹ ሰካራሞች ሁሉ ሆነች። እነዚህ ወንዶችና ሴቶች፡ እያንዳንዳቸው፡ በአዲስ ወይን ተሞልተው ነበር። እግዚአብሔር ያንን ፕሮግራሙ ቀይሮት ከሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጣታችሁን ቀስራችሁ አሳዩኝ፥ እዚያ የለም። የለም፡ ወዳጄ። እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ፡ እንዲሁ ነበር፡ እስከ መጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ድረስ፡ እና ኢየሱስ ሲመጣም ሁኔታው ያው ይሆናል።

139 ተመልከቱ! እነሱ በዚያ አዲስ የወይን ጠጅ ሰክረው ሳሉ፡ ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር ለሁላችሁም የሚሆን ሙሉ ጎሞር አስቀምጦ እንደሆነ እንይ። መልካም።

140 እዚህ ሁሉም በውጭ ቆመው ነበር፡ እና የቀድሞ ያ ፈሪው ሰባኪ ስሙ ጴጥሮስ የሚባለው፡ “ትንሹ ድንጋይ፡” ኢየሱስን እስኪክድ ድረስ በቦታው በጣም ደንግጦ የነበረው፡ እና ወደ ውጭ ወጥቶ የጸለየው፡ እርሱም ከእነሱ ጋር መሰብሰብ ተገባው። በሳጥን ላይ ወይም በሆነ ነገር ላይ ቆሞ፡ እንዲህ አለ፡ “እናንተ የይሁዳ ሰዎች፡ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ!” እነዚያም ዶክተሮች፡ ዲ.ዲ.ዎች ነበሩ። ኦህ፡ እንዲህ አላቸው፡ “እናንተ ሰዎች... እና የእስራኤል ሰዎች፡ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ፡ ሌሎቻችሁም፡ ይህ በእናንተ

ዘንድ የታወቀ ይሁን። ለእናንተ እንደመሰላችሁ፡ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፡ ከቀኑ ሶስተኛ ሰዓት ነውና። ይህ ግን… ”

141 ይህ ያ ካልሆነ፡ እኔ ያ እስኪመጣ ድረስ ይህንኑ መያዝ እፈልጋለሁ። ያ አንድ ነገር ነው።

142 እንዲህ አላቸው፡ “ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተነገረው ነው፡ ‘በመጨረሻዎቹ ቀናት እንዲህ ይሆናል፡ ይላል እግዚአብሔር፡ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ በሴቶችና በወንዶች ባሪያዎቼም ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፡ እነሱም ትንቢት ይናገራሉ፥ በላይ በሰማይ ድንቆችን፡ በታች በምድርም ምልክቶችን አሳያለሁ፥ የእሳት አምዶችና፡ ጭስና፡ ትነት፥ እንዲህም ይሆናል፡ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ፡ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል’።”

143 እነዚያ ራሳቸውን-አስጊያጭ፡ ባለ ረጅም-ካባ፡ ግብዞች የካህናት ወገን፡ እንዲህ አሉ፡ “እንድን ዘንድ ምን እናድርግ? ”

144 ጴጥሮስም፡ “ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ ለኃጢአታችሁ ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።” ለምን ያህል ጊዜ ነው? “ተስፋው ለእናንተና፡ ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው፡ በሩቅም ላሉት ሁሉ ነውና።”

145 ከዚያም፡ ንስሐ የገባና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተጠመቀ ሰው ሁሉ፡ እግዚአብሔርም የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ሲሰጠው፡ መጀመሪያ የወረደውን መና መሣይ ነገር አያገኛም፡ ነገር ግን፡ መጀመሪያ ከወረደው መና ጉርሻ ሙሉ ብቻ አያገኛም፡ ነገር ግን ከዚሁ ከመንፈስ ቅዱስ ልብ ሙሉ ያገኛል።

146 እናንተ ምናልባት፡ “ያንን ትንሽ ቀነስ አድርገው” ትሉኝ ይሆናል። በዚያ ላይ ትንሽ ድምፄን ከፍ ማድረጌን አውቃለሁ፡ ነገር ግን ዝም ማለት አልችልም። ልብ በሉ፡ እያችሁ። በእናንተ ላይ እየጮኽኩ አይደለም። ምናልባት እያስተጋባሁ ይሆናል። ነገር ግን፡ ኦህ፡ ልክ እንደ እኔ ቢሰማችሁ ኖሮ፡ እናንተም፡ ድምፃችሁን ከፍ ታደርጉ ነበር።

147 ልብ በሉ፡ ኦህ፡ በመጀመሪያ የወረደው የመጀመሪያው መና ልብ ሙሉ፥ በዚያን ጊዜ የወረደው ያው መንፈስ ቅዱስ፡ አሁንም እየወረደ ነው። ወዴትስ ይሄዳል? “ለእናንተ፡ ለልጆቻችሁ፡ በሩቅ ላሉት ሁሉ፡” ሉዊቪል፡ ኬንታኪ፡ “ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው ሁሉ፡ እኛ እዚህ የተቀበልነው ተመሳሳይ ነገር ይቀበላሉ።”

148 እሱ ያለው ይኸው ነው። እግዚአብሔር ይሄንን ባረከው። እሱ ሰበከው። መንፈስ ቅዱስ አመጣው፥ እኔ ተቀበልኩት፥ ያ ያጸናዋል። አሜን። ያ፡ ያ ለእኔ በቂ ነው። በቃሉ አመንኩት፥ እሱም አደረገው። እናንተም፡ ከፈለጋችሁት፡ ልታገኙት ትችላላችሁ። በትክክል።

149 ስለዚህ ከዚህ ከ—ከሞተ ሁኔታ ውጡና፡ ንቁ፡ ልክ እንደዚያ ያናውጣችሁና ያነቃችኋል። በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ዙሪያችሁን ስትመለከቱት ሁሉም ነገር የተለየ ሆኖ ይታያችኋል። ያ የማታነጋግሩት ሰው፡ ወደ እሱ ለመድረስና ለማነጋገር ትቸኩላላችሁ፥ አዎን፡ ወዳጄ፡ ዝም ብሎ እንዲሁ ታነጋግሩታላችሁ፡ በቃ። ኦህ፡ እነዚያ ሁሉ ነገሮች፡ እነዚያን የቀድሞ

የጎማ መፍቻ መሣሪያዎች ትመልሳላችሁ፡ እና ሁሉንም... ያን ጊዜ ከሆቴል የወሰዳችኋቸውን እነዚያን ነገሮች በሙሉ። ከጠረጴዛ ላይ የወሰዳችሁት የብር ዕቃ ዙሪያ የጠቀለላችሁት ያንን ፎጣ፥ ያንን ለመመለስ፡ ትቸኩላላችሁ። በእርግጥ ታደርጉታላችሁ። አዎ፡ ወዳጄ። በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ያደርጋችኋል። አሁንም ማርያምን ተመልከቱ። ኡህ፡ ማይ!

ቶሎ ማለት አለብን። በጥሩ ሁኔታ እየቀጠልን ነው።

150 እነዚያ ያኔ የጥንቱ-ዓይነት ስብሰባ ካደረጉ በኋላ፡ በምድረ በዳ ውስጥ፡ ሄዱ። አሁን በጉዞአቸው ላይ ናቸው። በቀጥታ ወደ ሲን ምድረ በዳ መሄዳቸው፡ እስከ ምድረ በዳው ድረስ መወሰዳቸው፡ እስከዚያች—እስከ መራራው ውኃ ምንጭ ድረስ መመራታቸው አያስደንቅም ወይ? እግዚአብሔር ልጆቹን ካዳናቸውና፡ በመንፈስ ቅዱስ ከሞላቸው በኋላ፡ ወዲያውኑ ወደ መራራ ውኃ ምንጮች ሲወስዳቸው አይገርማችሁም? አዎን። ፍቅሩን በድጋሚ ሊገልጽላቸው ስለሚፈልግ ነው። ልክ ነው። በእዚያ ደረሱ።

151 ታውቃላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስን ስታገኙ፡ ብዙ መሰናክሎችን ታስተናግዳላችሁ። “የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፡ እግዚአብሔር ግን ከሁሉ ያድናቸዋል።” ኃይሉንና ቸርነቱን ሊያሳያችሁ እንዲችል፡ እግዚአብሔር በትክክል፡ ከፊቱ አምጥቶ ያጋፍጣችኋል።

152 በኢየሩሳሌም እንደነበረው እንደሰማሁትም፡ የበጉን እግር እንደሚሰብረው እረኛ ታሪክ ነው። ሌሎች እንዲህ አሉት፡ “እንዴት፡ አንተ ጨካኝ እረኛ። የበጉን እግር ለምን ሰበርክ? ”

153 እንዲህም አለ፡ “መልካም፡ እኔን እንደምትወድ ባለማሳየቷ ነው። ስለዚህ ለየት ያለ ትኩረት እንድሰጣት፡ እግሯን እሰብራለሁ፡ ከዚያ በኋላ ትወደኛለች ብዬ አሰብሁ።”

154 አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር፡ በበሽታ በጀርባችሁ እንድትተኙ ሊያደርጋችሁ ይችላል፡ ዶክተሩም እንደምትሞቱ ይናገራችኋል። እግዚአብሔርን ትንሽ በበለጠ እንድትወዱት እግዚአብሔር ትንሽ ልዩ እንክብካቤ ሊያደርግላችሁ ይችላል። በትክክል።

> አንዳንዶች በውኃ ውስጥ፡ አንዳንዶች በጎርፍ ውስጥ፡
> አንዳንዶቹ በጥልቅ ፈተናዎች፡ ሁሉም ግን በደሙ፥
> ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ይመራል።

155 አሁን፡ እነሱ በዚያ በነበሩ ጊዜ፡ ውኃውም መራራ ስለነበር ሊጠጡት አልቻሉም ነበር፡ እግዚአብሔር መንገድ አዘጋጀ። አንዲት በባሕሩ ዳርቻ ላይ ተንጠልጥላ የነበረች ትንሽ ዛፍ፡ ሙሴ እንዲሁ ቆረጣትና ወደ ውኃው ውስጥ ጣላት፡ ሁኔታውን ሁሉ ቀየረው፥ ጥሩ፡ ጣፋጭ ውኃ።

156 አሁንም ከመራራ ውኃዎቻችሁ ውስጥ አንዱን፡ ወይም እንደዚያ ያለ ሌላ ነገር ሲያጋጥማችሁ፡ ዛሬ ምሽት፡ በመንፈሳዊ አነጋገር፡ ልትመሩባቸው የሚችሉትን፡ ማናቸውንም፡ መራራ ውኃዎች፡ የምታጣፍጥ፡ በጎልጎታ ላይ ወይም በዓለም ላይ የተንጠለጠለች አንዲት ዛፍ አለች። ልክ ነው። ቀራንዮ ማንኛውንም ሁኔታ ያጣፍጣል። ብዙ ጊዜ ወደ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንገባለን፡ እንዴት እንደሚሆንም እንገረማለን። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ዓይኖቹን

እጨፍንና፡ እንዲህ እሰባለሁ፡ “ቤዛዬ ስለ ሕይወቴ ደሙን ያፈሰሰበትና የሞተበት፡ እዚያ በጎልጎታ ላይ ነው፡” ከዚያም ፈተናዬ በጣም ትንሽ ሆኖ ይታየኛል። ወደ ጎን እተወውና እሄዳለሁ። ጣፋጭ ያደርገዋል። ያሳለፍኳቸውን ሁኔታዎች ሁሉ ያጣፍጣቸዋል። ወደ ማራ ውኃዎቼ በመጣሁ ጊዜ፡ እሱ ሁልጊዜ ያጣፍጠዋል።

157 አሁን፡ ከነዚያ ሁሉ ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች በኋላ፡ አሁን እዚህ በምድረ በዳ ውስጥ ልናገኛቸው ነው። ሪቫይቫሉ ጸጥ ብሏል። በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ሪቫይቫሉ ጸጥ ሲል፡ ወዲያውኑ፡ ስለ ተአምራቱ ሁሉ ረሱ።

158 ይህ በዛሬ ዘመን እንዳሉ ዓይነት ሰዎች አይደለምን? ባለፈው ዓመት እግዚአብሔር ያደረገውን ረሱት። እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረው ሰብሰባ ላይ ያደረገውን፡ እናንተ ፈጽማችሁ ትረሳላችሁ። አያችሁ? እግዚአብሔር ያደረገውን፡ በቀላሉ እንረሳዋለን።

159 አሁን፡ ልብ በሉ፡ እርስ በእርሳቸውም መከራከር ስለጀመሩ፡ “እንዴ፡ በእውነት፡ ከሁሉም በላይ፡ እኔ ሜቶዲስት ነኝ። የእኛ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ነው።” “እኔ ባፕቲስት ነኝ፡ አሁኑኑ እነግራችኋለሁ፡ እኛ በዘላላም ደህንነት እናምናለን፡ አግኝተነዋልም። ሃ፡ ሃ! በመሰረቱ፡ እናንተ’ኮ ትምህርቱም የላችሁም።” ወደ ችግር የምትገቡትና፡ የውኃ አቅርቦታችሁ የሚቋረጠው በዚያን ጊዜ ነው። በትክክል። በትክክል።

160 በምድረ በዳ ሲሆን፡ ያን ጊዜ፡ በምድረ በዳ መኖር ሲጀምር፡ ማጉረምረም፡ ማጉረምረም እና ቅሬታ ማቅረብ ይጀምራል። “እንዴ፡ እኔ እነግራችኋለሁ። እኔ ልንገራችሁ፡ ያ የድሮው ፓስተር እዚህ በነበረ ጊዜ፡ እንደዚያ ያለውን የቀድሞ-ዘመን ሃይማኖት የሰበከው ያ የቀድሞው ሰባኪ፡ እኔ—እኔ እሱ ትክክል ይሁን አይሁን አላውቅም። እኔ ልንገራችሁ፡ እሱ—እሱ አንድ ቀን ምሽት፡ እናቴን በጣም ሰላበሳጫት፡ ወደ ቤት ሄደች። እና፡ ልንገራችሁ፡ በጣም ተረብሻ ነበር።” መረበሽም ነበረባት። በትክክል። “ኦህ፡ ከእንግዲህ እኔ ያንን መስማት የምፈልግ እንደሆነ፡ አላውቅም።” እና የውኃ አቅርቦታችሁ የሚቋረጠው በዚያን ጊዜ ነው። በትክክል። ወደ ምድረ በዳ የምትገቡት በዚያን ጊዜ ነው።

161 ማጉረምረም ጀመሩ። እንዲህም አሉ፡ “ነፍሳችን—ነፍሳችን ይህንን ቀላል እንጀራ ተጸየፈችው።” የግብፅን ነጭ ሽንኩርትና ቀይ ሽንኩርት ትተው ከመጡ በኋላ፡ የመላእክትንም ምግብ እየበሉ ሳሉ፡ አሁንም ማማረር ነው። ይህ የቤተክርስቲያን ምሳሌ አይደሌምን? አሁንም ወደ ሆሊነስ ሰዎች እየመጣሁ ነው፡ ሁላችሁም፥ አዎ፡ ሁላችሁም። የመላእክትን ምግብ እየበሉ፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡ “አሁንም ነጭ ሽንኩርት ለመብላት፡ ወደ ግብፅ ተመልሰን በሄድን።”

162 “ክሌይተን ማክሚከንና ቡድኑ ዋይልድካትስ ዛሬ ማታ መጠጥ ቤት ሊገኙ ነው። ያቺን የቀድሞ፡ የሐይማኖት ተቋም ባልቀላቀል ኖሮ፡ በሄድኩ ነበር።” ብትሄዱ ይሻላል። መዝገባችሁ ባለበት፡ ልባችሁም በዚያ ይሆናል። ሲጀመርም ምንም አላገኛችሁም። ልክ ነው። ልክ ነው። “ኦህ፡ **ይህን** ማድረግ፡ ወይም **ያንን** ማድረግ በወደድኩ።” ይኸውላችሁ፡ ሁልጊዜ ማማረር።

163 ከዘላለም ዓለት የሚፈልቀውን ንጹህ ውሃ ለመጠጣት፡ የግብፅን የቆሸሸ ውሃ ትተው መጡ፡ ነገር ግን ስለ እርሱ ያማርሩ ነበር። ከታላቁ ባለ መድኃኒት

ጋር ለመሆን፡ የግብፅ ታላላቅና ትምክህተኞች፡ እጅግ ትምክሕተኛ ሐኪሞች ያሉበትን ስፍራ፡ ትተው መጡ። ማለትም፡ “የተአምራቶች ዘመን አልፏል፡” ከሚሉበት ስፍራ ወጥተው፡ ምልክቶችና ድንቆች ከሚከተሏቸው ህዝብ ጋር ለመሆን መጡ፡ ሆኖም አሁንም ያማርራሉ። ኦህ፡ ማይ! አዎን፡ ወዳጄ። በዚያ በግብፅ፡ በእርግጥም፡ ግብፃውያኑ፡ ቀዝቃዛ አሕዛብ፡ ግድ የለሾች ነበሩ። በተአምራት በሚባል ነገር አያምኑም ነበር።

164 ከዚያም፡ የእሳቱ ዓምድ በዙርያቸው በነበረበት በዚህ ስፍራ ነበሩ። ዛሬ ማታ እኛም አለን። በሰፈሩ ውስጥ ደስታ፡ እልልታ፡ ተአምራት የሚደረጉበትና፡ ሁሉም ነገር ባለበት ስፍራ ነበሩ፡ ዳሩ ግን ስለ እሱ ያማርራሉ። ውሃው የደረቀበት ምክንያት ያ ነው፡ የሚበሉትም ሆነ የሚጠጡት ያጡት በዚህ ምክንያት ነው፡ ምክንያቱም ያጉረመርሙ ነበር።

165 ዛሬ ማታ በሉዊስቪል ዙሪያ ባሉ የሐይማኖት ተቋማት ውስጥ ያለው ችግርም፡ ይኸው ነው፥ ማጉረምረም፡ ማማረር። አቤቱ ማረን! ወደ አገልግሎቱ ተመለሱ። በቃ።

166 “ከዚያም፡ ይህ ሙሴ የተባለው ሰው ማን ነው? ለመሆኑ፡ ለምን ሰማነው፡ ለምንስ የዚህን የሆሊ-ሮለር ስብከት ሰማን? እዚህ ውጭ ምን እያደረግን ነው? ” እናም የውሃ አቅርቦታቸውም ደረቀ።

167 ስለዚያ ታላቅ ሰው፡ ስለ ሙሴ አስባለሁ። እርሱ በሁሉም—በግብፃውያን ጥበብ የተማረ ሰው ነበር። ለጥቂት ደቂቃዎች እስቲ እንመልከተው። ሙሴን ለጥቂት ደቂቃ ብቻ፡ እንውሰደው። ያንን ሰው ተመልከቱት። እርሱ...

168 ግብፃውያን፡ ወደ ሕክምና ሳይንሳችን ስንመጣ፡ ዛሬ ከእኛ እጅግ የራቁ ነበሩ። ከእኛ እጅግ የራቁ ነበሩ። እኛ የማንችላቸውን ብዙ ነገሮች ማድረግ ይችሉ ነበር።

169 ሙሴም መፍትሔው ሁሉ ነበረው። እዚያ በነበረበት ጊዜም፡ አስቡት፡ ሙሴ ከሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ከእርሱ ጋር ነበረው። ትናንሽ ልጆች ነበሩት። ሽማግሌዎች፡ አሮጊቶች ከእርሱ ጋር ነበሩ። ሽባዎችና፡ እውሮች ነበሩት። በሳምንት ጊዜ ውስጥ፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት፡ ይወለዱ ነበር። ሙሴም፡ ዶክተር ሙሴ፡ ከነዚህ ሁሉ ህዝብ ጋር እዚያ በምድረ በዳ ነበር። ወደ መድኃኒት ሳጥኑ ውስጥ ማየት እፈልጋለሁ፡ እናንተስ አትፈልጉም? ዶክተር ሙሴ በመድኃኒት ሳጥኑ ውስጥ ምን እንደነበረው ማየት እፈልጋለሁ። እስቲ በመድኃኒት ሳጥኑ ውስጥ ምን እንደነበረው ጥቂት አሻግረን እንይ።

170 “ሙሴ ሆይ፡ ለመሆኑ፡ ሙሴ፡ እዚያ ውስጥ የያዝከው ምን ነበረ? ” ለምን ቢባል፡ በዚያ አርባ-ዓመታት ጉዞ ውስጥ፡ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሕፃናት እንደተወለዱ ደርሰንበታል። በትክክል። “ሙሴ ሆይ፡ ምን ተጠቀምክ? ለዚያ ሁሉ ስቃይና ሕመም፡ ካንሰር፡ ዕውርነት፡ ደንቆሮነትና ዲዳነት ምን ተጠቀምክ? ለምን ቢባል፡ ከምድረ በዳ ሲወጡ፡ በመካከላቸው አንድም ደካማ አልነበረም ብለው፡ ነግረውኛልና።” በሉ፡ አንዳንድ ዶክተሮች፡ ወደዚያ የመድኃኒት ሳጥን ውስጥ ማየት አያስፈልጋቸውምን?

171 “ሌላም ነገር፡ ሙሴ፡ ልብሳቸው እንኳ እስከማያልቅ ድረስ፡ በእነዚያ ህዝብ ላይ የረጨኸው ምን ነበር? በእነዚያ ዓለቶች ላይ ሲራመዱ፡ ጫማቸው ከቶ አላለቀም።” እዚያ ሄዳችሁ ካወቃችሁ፡ ምድረ በዳው ምን እንደሚመስል

ታውቃላችሁ፡ በሦስት ቀናት ውስጥ አንድ ጥንድ ጫማ ይጨርሳል። እነርሱ ግን በአርባ ዓመታት ውስጥ፡ ከቆዳው ላይ አንዲት ቅንጣት እንኳ አላረጁም። “ሙሴ ሆይ፡ በመድኃኒት ሳጥንህ ውስጥ ምን ነበረ? ”

172 እስቲ ወደ ውስጡ እንመልከት። እየዋለሁ፡ “አንድ የመድኃኒት ማዘዣ አገኘሁ፡ ‘እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝ።’” አለቀ ደቀቀ። አሜን።

173 እንዲህም አለ፡ “ኦህ፡ ሙሴ፡ አባቴ እዚህ ነበር፡ አሁን ወድቆ እግሩን ተሰብሯል። ለእርሱ ምን አለህ? ”

174 “እስቲ ልመልከትና ልይ። ‘ድምፄን ብትሰሙ፡ ያዘዝኩትንም ሁሉ ብታደርጉ፡ በግብፃውያን ላይ፡ ካደረስኩት በሽታ አንዱንም በእናንተ ላይ አላደርስም፡ ምክንያቱም እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝ።’ ይህንን ንገረው።” እርሱ ዳነ። አሜን። ልክ ነው።

“ኦህ፡ እርሱ በጣም ታሟል! ልጄ ሆድ ቁርጠት፡ ወይም የሳምባ ምች፡ በጣም ይዞታል! ዶክተር ሙሴ፡ ምን ማድረግ እችላለሁ? ”

175 “እስቲ ያለኝን ልይ። ‘እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝ።’” አለቀ ደቀቀ። አሜን። ሄዱ። ልክ ነው። እየተደሰቱ፡ ቀጠሉ። የሚያስፈልገው ያ ብቻ ነበር፡ “እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝ።”

176 ከስድስት መቶ በላይ የሚሆኑ፡ በአዲስ ኪዳን ብቻ የተሰጡ፡ ግልጽ የመለኮታዊ ፈውስ የተስፋ ቃላት እያሉ፡ ሆኖም ዛሬ ማታ፡ እግዚአብሔርን እንጠራጠራለን። ፍርዱ ለእኛ ምን ትርጉም ይኖረዋል? በትክክል።

177 “እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝ።” አዎን፡ ወዳጄ። ሙሴ የነበረው፡ ዶክተር ሙሴ በሱ አውድ ውስጥ፡ በሱ... በመድኃኒት ሳጥኑ ውስጥ የነበረው፡ ይህ ነው፡ “እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝ።” ስለዚህ በሽታዎችን ሁሉ ፈወሰ፡ ፍጹም በሆነ ሁኔታም ጠበቃቸው፡ በቀጥታም በምድረ በዳው በኩል፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር አመጣቸው። ኦህ፡ ማይ!

178 ከዚህ ታላቅ ባለ መድኃኒት ጋር ለመሆን፡ እነዚያን ሁሉ ትልልቅና፡ ትምክሕተኛ ሐኪሞች ትተው መጡ። ቀዝቃዛ፡ ደንታ ቢሶችና፡ ግድ የለሾች የነበሩትን ያንን ህዝብ፡ “ተአምራት የሚባል ነገር የለም” የሚሉትን፡ ትተው መጡ። ልክ እዚህም፡ የእሳት ዓምድ በላያቸው ላይ ተንጠልጥሎ ነበር። ህዝቡ እየተፈወሰ ነበር። የሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ፡ ማንኛውም ነገር፡ ለእነርሱ ቀርቦላቸው ነበር፡ ሆኖም ውሃ ሲያጡ ያማርሩ ነበር። ዳሩ ግን በዚያ ሁሉ ውስጥ፡ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ...

179 ልክ ዛሬ ማታ እዚህ በሉዊስቪል እንዳላችሁት፡ በዚህ ሁሉ እንዲህ በሚለው ጩኸት መካከል ናችሁ፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል። የሕክምና ማኅበሩ፡ በመላ አገሪቱ መለኮታዊ ፈውስን ለማስቆም እየሞከረ ነው።” በፍጹም አታቆሙትም። አሁን ብታቆሙ ይሻላል። ፀሐይን ማስቆም እንደማትችሉ ሁሉ ይህንንም ከቶ ልታስቆሙት አትችሉም። ልክ ነው።

180 በቅርቡ፡ ያኔ በመጀመሪያ በጄፈርሰንቪል ስጀምር፡ መለኮታዊ ፈውስን እሰብክ ነበር። በተግባር፡ ለዓመታት፡ ሳይታወቅ ቆይቶ ነበር። ከባድ ነገር ነበር። ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ ዛሬ ማታ፡ በየቦታው፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩት እየጮኹ

ነው። ለማሰቆም ትሞክራላችሁ? አትችሉም። "እኔ እግዚአብሔር ተክያታለሁ፥ ማንም ከእጄ እንዳይነጥቃት፡ ቀንና ሌሊት፡ አጠጣታለሁ።"

181 በቅርብ ጊዜ፡ በሰታቱ ኦፍ ሊብሪቲ ላይ ያሉ አንዳንድ ትናንሽ ድንቢጦችን እመለከት ነበር። ዝም ብለው እዚያ ተኙተው ነበር። ትናንሾቹ ፍጥረታት በብርሃኑ ስር፡ በሁሉም አቅጣጫ ተኙተው ነበር። መሪውንም፡ "ይህን ያደረገው ምንድን ነው? " አልኩት።

182 እርሱም እንዲህ አለ፡ "ትላንት ማታ፡ በነበረው ማዕበል ውስጥ፡ ጭንቅላታቸውን አጋጭተው ነው። ወደ ብርሃኑ መጡ፡ ብርሃኑም ወደ ሞቾት ይወስዳቸው ነበር፡ ነገር ግን ብርሃኑን ለማጥፋት ይሞክሩ ነበር። ብርሃኑን ለማጥፋት ሲሞክሩም፡ ጭንቅላታቸውን ፈረከሱ።"

183 እኔም "ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን፡" አልኩት! እብድ የሆንኩ መስሎት ሊሆን ይችላል። አልኩትም፡ "ይህ መለኮታዊ ፈውስን እና የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሳኤ ኃይል ለማጥፋት የሚሞክሩትን አንዳንድ ሰዎች ያስታውሰኛል።" ጭንቅላታችሁን ትፈረክሳላችሁ፥ እንጂ ከቶ አትችሉም። ዝም ብላችሁ ተቀበሉት፡ በውስጡም፡ ወደ እረፍት ግቡ። በትክክል። አሜን።

184 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፡ "ሙሴ ሆይ፡ ዓለቱን ተናገረው፡" "እርሱም ውሃውን ያወጣል፡ የእርሱን ውሃ ያወጣል።"

185 በቅርብ ጊዜ፡ በአንድ ሙዚየም ውስጥ፡ ይህ ዓለት ሲመታ የሚያሳይ ሥዕል እመለከት ነበር። ከእርሱም የሚወጣው ፈሳሽ፡ በጣም ትንሽ የሆነች የልብስ መስፊያ መርፌ የሚያክል ይመስል ነበር። አሰብኩም፡ "እነዚህ ሰዓሊዎች እንዴት እንዲህ ሊቀልዱ ይችላሉ!" ለምን ቢባል፡ ወንድሜ፡ በጣም ጠምቶኝ ቢሆን ኖሮ ያንን ነገር እስኪደርቅ ድረስ እጠጣው ነበር። አዎን፡ ወዳጄ።

186 ሙሴ ከዚያ ዓለት መጠጣት እንደነበረበት ታውቃላችሁ? ከእንስሳቱ ሁሉ በተጨማሪ፡ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ህዝብ ነበረው። እነርሱን፡ ለ—ለ ለማጠጣት፡ በደቂቃ ወደ አርባ ሺህ ጋሎን ያህል ይወስድ ነበር። ሃሌሉያ!

187 ያ በሐይማኖቱ ውስጥ ያለውን አንድን ሰው ያስታውሰኛል። እሁድ ጠዋት ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ለመሄድ የሚያበቃ ሃይማኖት ብቻ ነው ያላችሁ፡ ልክ ጥቂት ጠብታ እንደረጨባችሁና ትንሽ እንዳረጠባችሁ ያህል ነው።

188 እኔ ጅረቶች በሚወጡበት ምንጭ አጠገብ መቀመጥ እወዳለሁ፡ ሃሌሉያ፡ እስከ ዘላለም ሊያደርሰኝ የሚበቃ። ሃሌሉያ! ከዚያ የቀድሞ የእርጥበት ቦታ ወጥቼ፥ ሁልጊዜ ወደሚፈስበት ምንጭ ስለተዛወርኩ ደስ ብሎኛል። አዎን፡ ወዳጄ።

189 ሰዎች ያላቸው እነርሱን ምስኪኖች ለማድረግ የሚያስችል በቂ ሃይማኖት ብቻ ነው። "እንግዲህ፡ እኔ ከአሥር ደቂቃ በላይ መቀመጥ አልችልም። ወይኔ፡ አምላኬ፡ ሰባኪው እንዴት ያለ ረጅም ንግግር ነው የሚያደርገው? " ደህንነታችሁ ምን ያህል ጥልቅ ነው? በትክክል።

190 እሁድ ጠዋት ትወጣላችሁ፡ እንዲህም ትላላችሁ፡ "እንግዲህ፡ ወጥቼ የሚሉትን እሰማለሁ።" አንድ ትንሽ ጠብታ አግኝታችሁ ትመለሳላችሁ፡ ያላችሁም ያው ብቻ ነው።

191 ወንድሜ፡ እነግርሃለሁ፡ ሙሴ ያንን ዓለት በመታው ጊዜ፡ መላውን ምድረ በዳ አጠጣ። አሜን። አዎን፡ ወዳጄ። ብቸኛው ነገር፡ ያስፈለጋቸው ነገር ሁሉ፡ ዝም ብለው ወደቁና እስኪጠግቡ ድረስ ጠጡ፡ ጠጡ፡ ጠጡ። አሁንም፡ በደቂቃ አርባ ሺህ ጋሎን ያህል፡ ተጨማሪ ውሃ ይመጣ ነበር። ስንት ህዝብ፡ የተጠሙ ህዝብ፡ ከግመሎቹ፡ ከእንስሳቱና ካላቸው ነገሮች በተጨማሪ፡ አንድ ሚሊዮን ህዝብ፥ ሁለት ሚሊዮን ህዝብ፡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ ሊጠጡ እንደሚችሉ፡ አስሉት። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ አለ፡ "በተትረፈረፈ ሁኔታ ወጣ።" በምድረ በዳው ውስጥ፡ በጩኸት ፈሰሰች።

ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን የሚሰጠው በዚህ መንገድ ነው።

192 ዝም ብሎ ለጥቂት ብቻ፡ እንዲህ ለማለት አይደለም፡ "እንግዲህ፡ ሄጄ ቤተክርስቲያንን እቀላቀላለሁ ብዬ አምናለሁ።" ኦህ፡ ማይ! "ኦህ፡ ያንን ጩኸት መቋቋም አልችልም። ብርድ ብርድ ይለኛል።" መቼም ብትሞቱ፡ ወደ ሰማይ ብትገቡ በቅዝቃዜ ትሞቱ ነበር፡ ምክንያቱም፡ ወንድሜ፡ እዚያ ስትደርስ አንዳንድ ጩኸቶችን መስማትህ አይቀሬ ነውና። መጽሐፍ ቅዱስ በቀንና በሌሊት "ሃሌሉያ፡" እያሉ ይጮኻሉ ይላል፥ ቀኑን ሙሉ፡ ምክንያቱም ሌሊት የለምና። ልክ ነው። እዚያ ሰማይ በደረስክ በሁለተኛው ቀን፡ በእርግጠኝነት ትሞታለህ። አዎን፡ ወዳጄ። እንግዲህ፡ አንተ ዝም ብለህ... ያደረግከው፡ ዝም ብለህ ሄድክና፡ ትንሽ ረጠብክ ብቻ ነው።

193 በዚያ ምንጭ አጠገብ ለምን አትቀመጥም ወይ፡ ከዚያም ወደ ሆነ ነገር አጥባ እስክታወጣህ ድረስ... ሃሌሉያ፡ ወደ መካከል ውስጥ እስኪያወጣህ ድረስ፡ እራስህን እስክታጣና የት እንዳለህ እስኪያጠፋህ ድረስ እንዲፈስልህ ለምን አታደርግም። [በቴፕ ላይ ያለ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] መሆን ያለብህ በዚህ መንገድ ነው።

194 በዩቲካ ፓይክ ላይ እዚህ ካለው ከዚህ ትንሽ ኩሬ ጋር በተያያዘ፡ ለአጎቴና፡ ለአባቴ፡ "ኧረ፡ እኔ መዋኘት እችላለሁ" እላቸው ነበር።

195 አንድ ቀን፡ አባቴ ሄደና መውረጃው ላይ ተቀመጠና እንዲህ አለኝ፡ "ስትዋኝ ማየት እፈልጋለሁ።" ትንሿ ኩሬ ጥልቀቷ **ይህን** ያህል ነበር። በአንድ ሳጥን ላይ ቆሜ ነበር። ልብሶቼን አወለቅኩና፡ አፍንጫዬን **እንደዚህ** ይዤ፡ በሳጥኑ ላይ ወደ ላይ-እና-ወደ ታች ዘለልኩ። ውስጥ ሰገባ፡ ጭቃው ወደ ሁለቱም አቅጣጫዎች በረረ፡ ጭቃውንም መርጨት ጀመርኩ።

አልኩትም፡ "አባዬ፡ እንዴት እያደረግኩ ነው? "

196 "ከዚያ ውጣ፡" አለኝ። መዋኘት? ሁልጊዜ፡ ጭቃን ማንቦጫረቅ።

197 እኛም፡ ጭቃ-የሚያንቦጫርቁ ብዙ የቤተክርስቲያን አባላት አሉን። ልክ ነው። ልክ ነው፡ ጭቃ-አንቦራጫቂዎች። አዎ፡ ወዳጄ።

198 አንድ ቀን፡ አጎቴ በጀልባ አወጣኝና ስለ መዋኘት እፎክር ነበር፥ እዚህ በኦሃዮ ወንዝ ውስጥ፡ ሃያ ጫማ ያህል ጥልቀት ያለው ውሃ ነበር። እርሱም በመቅዘፊያው እንዲሁ ወደ ውሃው ውስጥ ገፋኝ፡ እንዲህም አለ፡ "አሁንስ ምን ትላለህ? " አሜን። ሃሌሉያ! ያን ጊዜ፡ መዋኘት ወይም መስመጥ ነበረብኝ። ኦህ፡ ማይ!

199 አሁን ብትለምዱት ይሻላል። እግዚአብሔር እዚያ በምድረ በዳ ዓለቱን ከፍቶ ዝም ብሎ ባፈሰሰበት፡ በዚያ ምንጭ ውስጥ ያውጣችሁ። “ዓለቱን ተናገረው፡” አለ እርሱ፡ “እርሱም የገዛ ውሃውን ያወጣል።”

200 ምናልባት፡ ወዳጄ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ምናልባት እየጠፋህ ሊሆን ይችላል። ዓለቱን ልትናገረው ይገባል። ልክ ነው።

201 ምናልባት በየቦታው ሄዳችሁ ይሆናል። ምናልባት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ፡ ከሜቶዲስት አባል ሆናችሁ፡ ባፕቲስት ተቀላቅላችሁ ይሆናል፥ በተቆጧችሁ ጊዜም፡ ወደ ፕሬስቢቴሪያን ሄዳችሁ ይሆናል፥ ደግሞም ወደ ጴንጤቆስጤ፡ ወደ ናዝሪን፡ ዝቅ ብሎም ወደ ፒልግሪም ሆሊነስ ተመልሳችሁ ይሆናል። ሆኖም አሁንም ያለምንም ማስተዋል ናችሁ።

202 ዛሬ ማታ፡ እንዲሁ ዓለቱን ተናገሩት። ዝም ብላችሁ… ከእርሱ ጋር የመነጋገር ልምምድ አላችሁን? አዎን። እርሱም እንዲህ አለ፡ “ዓለቱን ተናገሩት፡ እርሱም የገዛ ውሃውን ያወጣል።” የገዛ ውሃውን ያወጣል፡ እንዲሁ… ዳግመኛ ልትመቱት፡ አያስፈልጋችሁም። እንዲሁ ተናገሩት። እንዲሁ በወዳጅነት መንፈስ፡ ተናገሩት።

203 ምናልባት ወደ ሐኪም ሄዳችሁ ይሆናል። ምናልባት ለመዳን ስትሉ፡ ማድረግ የምትችሉትን ሁሉ አድርጋችሁ ይሆናል። ምናልባት በሙሉ ኃይላችሁ ማድረግ የምትችሉትን ሁሉ፡ አድርጋችሁ ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን ልትድኑ አልቻላችሁም። በምታውቁት፡ በእያንዳንዱ የሐኪም ቢሮ ውስጥ አልፋችሁ ይሆናል፡ ሐኪሙም እንዲህ ብሏችኋል፡ “እንግዲህ… ለአንተ ሊደረግ የሚችል ምንም ነገር የለም።” ታዲያ፡ ዛሬ ማታ ለምን ዓለቱን አትናገሩትም? እርሱ… ለአንተ የሚሆን የሕይወትን ውሃ አለውና፡ እርሱ አብዝቶ ይሰጥሃል።

204 አንድ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ አጋር የምትባል፡ አንዲት ሴት ነበረች። ስለ እርሷ እያሰብኩ ነው። ጊዜው ስለደረሰ ልጨርስ ነው፥ ሰዓቱ። አጋር የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፡ አንድ ትንሽ ሕፃንም ነበራት። ከአንዲት ትንሽ የውሃ ማሰሮ ጋር፡ ወደ ምድረ በዳ ተሰደደች። ያንን ትንሽ ፍጥረት፡ ቀኑን ሙሉ አጠጣችው። ነገር ግን በቀትር አካባቢ፡ ውሃው አለቀ፡ ትንሹም ሕፃን ይጮኽና ያለቅስ ነበር። ትናንሽ ከንፈሮቹ ደርቀው ነበር ምላሱም ያብጥ ነበር። አንዲት ምስኪን፡ አዛኝ-እናት፡ ምን ልታደርግ ትችል ነበር? ጥቂት ውሃ ለማግኘት፡ የምትችለውን ቦታ ሁሉ ፈለገች፡ ነገር ግን ምንም ውሃ ሊገኝ አልቻለም። ሕፃኑ ሲሞት ማየት አልቻለችም፥ ስለዚህ በአንድ ቁጥቋጦ ስር አስቀመጠችው፡ የቀስት-ውርወራ ያህልም ርቃ ሄደች።

205 ተንበረከከችም ዓለቱንም ተናገረችው። ዓለቱን በተናገረች ጊዜ፡ አንድ መልአክ መለሰላትና እንዲህ አላት፡ “አጋር ሆይ፡ እዚያ ማዶ የሚፈልቀው ምንድን ነው? ”

206 በዚያም ዛሬም ድረስ የሚፈስ፡ በውሃ የተሞላ፡ ሙሉ ጉድጓድ ነበረ። ከአራት ሺህ ዓመታት በኋላም ቢሆን፡ ዛሬም ድረስ እየፈሰሰ ነው። በዚያ የነበረው… ያ የአጋር ምንጭ፡ ያ፡ ዛሬም ድረስ እየፈሰሰ ነው። እርሷ ዓለቱን ተናገረችው፡ ዓለቱም ውሃውን አመጣ።

207 አንድ ቀን፡ ወደ እሳት እቶን ውስጥ የገቡ አንዳንድ የዕብራውያን ልጆች ነበሩ፡ እነርሱም ዓለቱን ተናገሩት። ዓለቱም ከእነርሱ ጋር ነበረ።

208 በአንድ ወቅት፡ ከሰማርያ የመጣች አንዲት ሴት ነበረች። ተሰፋ ቆርጣ ነበር። ኃጢአተኛ ነበረች፡ ምናልባትም፡ በሕይወቷ ላይ የተንጠለጠሉ ብዙ ነገሮች ነበሩባት። ተሰፋም ቆርጣ ነበር። ለዕረፍት ወደ ያዕቆብ ጉድጓድ እየሄደች፡ ትመለሰም ነበር። ወደ ያዕቆብ ጉድጓድ ትሄድና፡ ትመለሰም ነበር። አንድ ቀንም እንስራዋን አስቀመጠችና፡ ተሰፋ ቆርጣ፡ እዚያ ቆማ ነበር። እዚያም፡ ዓለቱ ከጎኗ ቆሞ ነበር። ያንን ዓለት ተናገረችው። እርሱም በነፍሷ ውስጥ ታላቅ ምንጭ ሰጣት። ወደ ከተማዋ ሮጠች። ከዚያ በኋላ፡ ለመቅዳት ከቶ አልመጣችም። ሕይወት ነበራት። እንዲህም አለች፡ "ኑና፡ ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው እዩት። ይህ ክርስቶስ አይደለምን? " ዓለቱን ተናገረችው፡ ዓለቱም የገዛ ውሃውን አወጣ።

209 ገንዘቧን ሁሉ የወሰዱባት፡ በሐኪሞች፡ በባህላዊ አዋቂዎች ላይ ገንዘቧን ሁሉ የጨረሰች አንዲት ምስኪን ሴት ነበረች። የደም መፍሰሱን ማቆም አልቻለችም ነበር። ምናልባት እርሻዋን አስይዛ፡ ወይም ደግሞ ሸጣው ሊሆን ይችላል። አንድ ቀንም ተቀምጣ፡ እየፈተለች ሳለ፡ አንድ ነገር በመንገድ ላይ ሲመጣ ሰማች። ዓለቱን ተናገረችው። ዓለቱም ዘወር አለና እንዲህ አለ፡ "የነካኝ ማን ነው? " ዓለቱን ስትናገረው ሁሉም ነገር አበቃ። እርሱም የደም መፍሰሱን የሚያስቆም፡ የሕይወት ምንጭ ሰጣት። ወዲያውም፡ ደረቀ።

210 አንድ ቀን፡ በግንቡ አጠገብ ቆሞ በብርድ የሚንቀጠቀጥ፡ አንድ ዕውር ለማኝ ነበረ። የነበረው ነገር ሁሉ አልቆ ነበር። እነሆ እርሱ፡ ምስኪንም ሰው ነበረ፡ ሰዎችም በአጠገቡ ያልፉ ነበር። አንድ ነገር ሲመጣ ሰምቶ፥ "ምንድን ነው፡" አለ? ዓለቱንም ተናገረ።

211 ምንም እንኳ፡ በዙሪያው የነበሩት፡ የሐይማኖት ተቋም አባላቱ፡ እንዲህ በማለት፡ ሊያስቆሙት ቢሞክሩም፡ "ምንም ፋይዳ የለውም። ልታገኘው አትችልም። ዞር በል። ዝም በል።"

212 ነገር ግን እርሱ አብዝቶ ጮኸ፡ "የዳዊት ልጅ ሆይ፡ ማረኝ! ማረኝ!" ዓለቱንም ተናገረ፡ ዓለቱም ምንጭ ሰጠው፡ ዓይኖቹም ተከፈቱ።

213 ያ በምድረ በዳ የነበረው ያው ዓለት ዛሬ እዚህ አለ። ህዝቡንም ደሰ እንዲላቸው ያደርጋል።

214 በአንድ ወቅት፡ መላ ኢየሩሳሌም አንድ መለኮታዊ ፈዋሽ ለማየት፡ አንድ ሆሊ-ሮለር፡ ወደ ከተማ ሲገባ ለማየት ቆማ ነበር፥ ጥቂት ህዝብ እዚያ ቆመው በታላቅ ድምፅ፡ እንዲህ እያሉ ይጮኹ ነበር፡ "ሆሳዕና! በጌታ ስም ለሚመጣ፡ ሆሳዕና!"

215 እነዚያ ራሳቸውን-የሾሙ የቤተ ክርስቲያን አባላት ረጅም ልብሳቸውን ለብሰው፡ ዲ.ዲ የሚል ማዕረግ የተጫኑ የሐይማኖት ተቋም አባላት በዚያ ነበሩ፥ እንዲህም አሉ፡ "ዝም እንዲሉ አድርጋቸው። ኧራ፡ ጀርባዬ ላይ ብርድ ብርድ እንዲለኝ ያደርጉኛል፡ ወዘተ። ዝም እንዲሉ አድርጋቸው።"

216 እንዲህ አለ፡ "እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች፡ ወዲያው ይጮኻሉ።" ለምን ነበር? ያ ያለ እጅ፡ ከተራራው የተፈነቀለው ዓለት፡ እየተንከባለለ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣ ስለነበር ነው። ትናንሾቹ ዓለቶች ከእርሱ ይጠጡ ነበር። "ዓለቱን ተናገሩት፡ እርሱም የገዛ ውሃውን ያወጣል።"

217 ዛሬ ማታ፡ ደህንነት ካስፈለጋችሁ፡ ዓለቱን ተናገሩት። እርሱም የገዛ ውሃውን ያወጣል። ዛሬ ማታ፡ ኰብላይ ከሆናችሁ፥ ዓለቱን ተናገሩት፡ እርሱም የገዛ ውሃውን ያወጣል። ዛሬ ማታ፡ እዚህ ሆናችሁ፡ ያለ ክርስቶስ ካላችሁ፥ ደህንነትን ለማግኘት፡ በከተማው ያለውን፡ እያንዳንዱን የሐይማኖት ተቋም ሞክራችሁ ከሆነ፥ ዓለቱን ተናገሩት፡ እርሱም ውሃውን ያወጣል። ታምናላችሁ? ከእግዚአብሔር የራቃችሁ፡ ኰብላይ ከሆናችሁ፡ ለእናንተ ምንም ዕድል የሌለ ከመሰላችሁ፥ ዝም ብላችሁ ዓለቱን ተናገሩት፡ እርሱም የገዛ ውሃውን ያወጣል።

218 ያንን በሙሉ ልባችሁ፡ ታምናላችሁ? እግዚአብሔር ይህን ያደርግልኛል ብላችሁ ታምናላችሁ? በሙሉ ልባችሁ፡ ታምኑታላችሁ? ሃሌሉያ! እርሱ ዛሬ ማታ እዚህ አለ።

219 የታመማችሁም ከሆናችሁ፡ በዓለም ያለውን ሁሉ ሞክራችሁ ከሆነ፡ በጸሎት መሰመር ውስጥ ለመግባት ሞክራችሁ፡ መግባት ካልቻላችሁ፥ የጸሎት ካርዶች ኖሯችሁና፡ ውድቅ ተደርጎባችሁ ከሆነ፥ ወደ አንዱ አገልግሎት ሄዳችሁ፡ ወደ ሌላው አገልግሎት ሄዳችሁ ከሆነ፥ በፓስተሩ ተቀብታችሁ ከሆነ፥ **በዚህ** የጸሎት መሰመር አልፋችሁ ከሆነ፥ በሌላ በማንኛውም ቦታ ሄዳችሁ ከሆነና፡ ልትፈወሱ ካልቻላችሁ፡ አሁን ለምን ዓለቱን አትናገሩትም? እርሱም ውሃውን ያወጣል። ልክ ነው። ለምን አንድ ጊዜ አትሞክሩትም? እርሱ አሁን እዚህ ሕንፃ ውስጥ እያለ፡ አሁኑኑ፡ ከእርሱ ጋር ንግግር አድርጉ።

220 የእርሱ መገኘት እያንዳንዳችሁን ለመፈወስ አሁን እዚህ አለ። አምናለሁ፡ በሙሉ ልቤ አውቀዋለሁ። አምናለሁ በ... የማላውቃቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፡ ነገር ግን የማውቃቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እዚህ መሆኑን አውቃለሁ።

221 አሁኑኑ፡ በልቤ ጥሪ ለማድረግ ልሞክር እያለሁ እንኳ፡ ራእዮቹ አሁን—— አሁኑኑ በሕንፃው ሁሉ ላይ እየታዩ ናቸው። ኦህ፡ ልክ ነው። የእግዚአብሔር ኃይሎች ልክ እዚህ አሉ። ልክ ነው። እዚህ ሲንቀሳቀስ አየሁት። አሁኑኑ፡ ከአንድ አድማስ ወደ ሌላው ሊያሻግረኝ ጀምሯል፥ ምክንያቱም እዚህ የታመሙ ሰዎች አሉ፡ ይህንንም እያደረገ ያለው የእናንተ ጸሎት ነው፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለማጽናት፡ ዛሬ ማታ፡ እርሱ ሊናገረው እዚሁ መሆኑን እየተናገረ ነው፡ ያው ቆሞ ሐሳባቸውን የተረዳው ዓለት እርሱ አለ። የደም መፍሰስ የነበረባት ሴት፡ የት እንደነበረች አይቷል፡ ወዘተ። እርሱ አሁን እዚህ ነው። ብትናገሩት፡ እርሱ የራሱን ውሃውን ያወጣል። በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ?

222 ምን ትያለሽ፡ እመቤት? በዚያ... ልክ በመሃል ላይ። አሁን፡ ምንም የጸሎት ካርድ የለሽም፡ አይደል? በዚያ ተቀምጠሽ፡ በአንገትሽ ዙሪያ ነጭ ነገር ያለሽ እመቤት። ስኳር በሽታ አለብሽ፡ አይደል? የጸሎት ካርድ የለሽም፡ አይደል? ምንም የጸሎት ካርድ አያስፈልግሽም። ያንን ታምኚያለሽ? ዓለቱን መናገር የምትችዪ ይመስልሻል? አሁኑኑ፡ ስለ ስኳር በሽታሽ፡ እርሱን መናገር ትፈልጊያለሽ? እንግዲያውስ በእግሮችሽ ቁሚ። ልክ ነው? ዝም ብለሽ፡ “አሁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ፈዋሼ እቀበላለሁ” በዪ፡ እግዚአብሔርም ወደ ቤትሽ ይወስድሻል እንዲሁም ያድንሻል። ዓለቱን ተናገሪው። እግዚአብሔር ይባርክሽ። መልካም ነው። ሂጂና፡ ተፈወሺ።

223 አንቺስ ምን ትያለሽ፡ እመቤት፡ ከእርሷ አጠገብ የተቀመጥሽው? በእግሮችሽ ላይ ቫሪኮስ የደም ስር አለብሽ፡ አይደል? አዎን። በእግሮችሽ ቁሚ። እዚያ አጠገብሽ የተቀመጠው ባለቤትሽ አይደለም? ልክ ነው? አንተም፡ ስኳር በሽታ አለብህ፡ አይደል? ልክ ነው? እጅህን በሚስትህ ላይ ጫን። መልካም ነው። ሁለታችሁም ከኢሊኖይ ናችሁ። ልክ አይደለም? አሁን ዓለቱን እያናገራችሁ፡ ወደ ኢሊኖይ ተመለሱ፡ ደዌው ይለቃችቀዋል እንዲሁም ዳግመኛ ከቶ አይመለሰም። ሃሌሉያ!

224 አንድ ነገር አውቃለሁ፡ ዓለቱ እዚህ መሆኑን፡ ያ በምድረ በዳ የተመታው የዘላለም ዓለት። ልክ ነው።

225 አንቺስ ምን ትያለሽ፡ በዚያ ባርኔጣሽ ላይ አበቦች ያሉሽ እመቤት? የመገጣጠሚያ ቁርጥማት ኖሮብሽ፡ ለመዳን እየሞከርሽ እዚያ የተቀመጥሽው። ወደ ሌላ አቅጣጫ ዘወር ብለሽ ያየሽው፡ እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? እንግዲያውስ በእግሮችሽ ቁሚ፡ እግሮችሽንም ወደ ላይ-እና-ወደ ታች አረጋገጪ፡ እንዲሁም "ቁርጥማቱ ሄዷል፡" በዪ፡ ደግሞም እንደዚያው ይሆናል። ዓለቱን ተናገሪው፡ እርሱም ያወጣል... ? ...

226 እነግራችኋለሁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም፡ ያው ነው። እርሱ ማንኛውንም ነገር ግልጽ ለማድረግ እዚህ አለ...

227 እዚያ የተቀመጥሽው፡ እመቤት፡ "ጌታ ይመስገን" ያልሽው፡ ያ የሴት ችግር ያለብሽ፡ ያን ትንሽ፡ አረንጓዴ-መሳይ ጃኬት የለበሽው፡ እዚያ የተቀመጥሽው እመቤት፡ ስለ እሱ ምን ታስቢያለሽ? በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እንደፈወሰሽ ታምኛለሽ? ለአንድ ደቂቃ፡ ያህል ቁሚ፥ ልክ እዚያ የተቀመጥሽው። በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? የሴቶች ችግር አለብሽ። እባጭ ነው። መውረጃም አለው፡ ከእሱ የሚወጣ የሆነ ዓይነት ፈሳሽ አለ። ልክ አይደለም? ያ ልክ ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ። ይህን እንድል ያደረገኝ ምንድን ነው? ዓለቱ ለአንቺ እየተናገረሽ ነው። መልሰሽ ተናገሪው፡ ደግሞም ተፈወሺ። ሃሌሉያ!

228 ኦህ፡ የኃይሉን መገለጫዎች ማሳየት እጅግ ይፈልጋል! አሁንም በምድረ በዳ ልጆቹን የተከተለውን፡ ያንኑ የእሳት ዓምድ የእግዚአብሔርን መልአክ፡ አሁን በዚህ ሕንፃ ውስጥ ሲንቀሳቀስ አየዋለሁ።

229 አንዲት ሴት ለማግኘት እየሞከርኩ ነው። እርሷ እየጸለየች ነው። እዚህ የት አለች? እነሆ እርሱ እዚህ ቆሟል። አዎ፡ እዚያ የቆመች አንዲት ትንሽ ሴት ናት፡ ሁለተኛዋ ረድፍ ላይ የተቀመጠችው። አይደለም፡ እርሷ... ስለ አንድ ሰው ነው፡ የቆመ። እየጸለይሽለት ያለሽው ሰካራም ባል ነው። ልክ አይደለም፡ እመቤት? ከሆነ፡ ልክ ባለሽበት በእግሮችሽ ቁሚ። እየጸለይሽለት ያለ ሰካራም ባል የለሽም? ያ ልክ ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ። ዓለቱን ተናገሪው፡ እግዚአብሔርም ከእዚያ—ከእዚያ ነገር ውስጥ ያወጣዋል።

230 እናንተ ብቻ አናግሩት እንጂ፡ እግዚአብሔር እዚህ ማንኛውንም ነገር ያደርጋል። ታምኑታላችሁ? ከእርሱ ጋር እየተነጋገራችሁ ነውን? ከሆናችሁ፡ አሁኑኑ በእግሮቻችሁ ቁሙና ዓለቱን ተናገሩት፡ ዓለቱም፡ የራሱን ውሃውን ያወጣል። ትቆማላችሁ?

231 ለመዳን የሚፈልገው ማነው? እጅህን አንሳና፡ "ወደ ልቤ እንዲገባ እፈልጋለሁ፡" በል። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክህ።

እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ አንተንም፡ አንተንም፡ አንቺንም ይባርክሽ። ኦህ፡ ማይ! አዎን፡ ወዳጄ።

232 ያ ካንሰር እዚያው ትቶሃል፡ ወንድሜ። ጠፍቷል። ወደ ቤትህ ሄደህ አሁን ደህና መሆን ትችላለህ። ሃሌሉያ! እውነት ነው።

233 መፈወስ የምትፈልጉ ሁሉ፡ እጃችሁን አንሱና፡ እንዲህ በሉ፡ “ጌታ ሆይ፡ እነሆኝ እየተናገርኩህ ነው። እነሆኝ እየተናገርኩህ ነው።” ልክ ነው።

234 ይኸው ለቆ ሄደ። ጌታዬ፡ ሳይነሰህ እዚያው ትቶሃል። ነፃ ነህ። ወደ ቤትህ ሂድ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ተፈውሰሃል።

235 እዚህ ያላችሁ፡ አሁን እርሱን ማግኘት የምትፈልጉ ማንኛችሁም፡ እጃችሁን አንሱና እንዲህ በሉ፡ “ጌታ ሆይ፡ ስለፈወስከኝ፡ አመሰግንሃለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ትፈውሰኛ ዘንድ፡ እየተናገርኩህ ነው።”

236 እግዚአብሔር ሆይ፡ የምሕረት አምላክ ሆይ፡ እርሱ አሁን በዚህ ሕንፃ ውስጥ እያለ፡ በዚህ ህዝብ ላይ እንዲያልፍ፡ ዛሬ ማታ ከመንፈስ ቅዱስ ቅባት ጋር፡ ኃይልህን ላክ። መንፈስ ቅዱስም እያንዳንዱን ተአምር ያድርግ። ዛሬ ማታ በሕንፃው ውስጥ አንድም የታመመ ወይም ሽባ የሆነ ሰው እንዳይቀር። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እያንዳንዱን ፈውስ።

54-0330 ቤዛነት በሙላት፡ በደስታ
ቸርች ኦፍ ዚ ኦፕን ዶር
ሎይስቪል, ኤንታኪ ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org